# የገበታ ወጎች

(ከፍቅር ካፌ)

ዓለማየሁ ማሞ

(ዋሽንግተን ዲ ሲ)

2007 (2014)

የገበታ ወጎች

ኮፒ መብት © 2007 ዓለማየሁ ማሞ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ

Dining table talks

Copyright © **2015** Alemayehu Mammo

All rights reserved

United States of America

ISBN 978-1-61119-130-1

ለማንኛውም አስተያየት

alexwrites@hotmail.com

ወይም

301 618 9596

# ማውጫ

መነሻ ነጥቦች.....5

1) ምስጋና መልካም ነው!.....9
2) መጀመሪያ መቀመጫዬን.....10
3) ለላምህን ያዝ.....11
4) የሰልት ቅያሪ.....12
5) ለው ለለው.....13
6) አረኛውን ማወቅ.....15
7) ከዶሮች ጋር የዋለው ንሰር.....17
8) ይቅርታን እንምረጥ.....18
9) ለፍራህን አትልቀቅ.....20
10) አባቴ ገመዱን ይያዝ!.....22
11) ዶሮዋ በከተማ.....23
12) ይለጣል እንጂ አይሸጥም.....25
13) የባሰ አለ.....26
14) ንጉሡን አሳዩኝ!.....28
15) ይቅር ተብያለሁ!.....30
16) ወደ የት ነው?.....33
17) ልናይ ኋላ.....34
18) የሚጠብቀን አይተኛም!.....36
19) ቀበሮ መጣ!.....39
20) የሰው ሰውነቱ.....41
21) ሁሉን ለማስደሰት.....43
22) ንጉሥ አይሳሳቱም.....45
23) አልተውህም አልለቅህም.....46
24) ለሚመጣው ትውልድ.....49
25) እኛኮ አልደረስንም.....50

26) ስንፍና አይገባም.............................5?
27) ወሬኛዋ ዔሊ.................................54
28) አሳዛኝ ተጓዥ.................................56
29) ፈጣሪህን አሳየኝ...........................59
30) ሁሉ ሰበብ.....................................62
31) ጥንቸልና ዔሊ.................................64
32) እንደ ስምህ ሁን.............................66
33) የጣቶች ፉክክር.............................68
34) ፕሮፌሰሩና ጀልበኛው ...............72
35) የባሰ ተአምር!.................................73
36) ከትሉ ላሰማነስ.............................75
37) ይቅርታ ፈላጊዎች.........................77
38) ዘወር በልልኝ.................................78
39) አስራሰሁ፤አታስሪም.....................80
40) የዘመናት ልፋት.............................82
41) ተነጥላ የሄደችው በግ...................84
42) ሁሰቱ እናቶች...............................87
43) ይድረስ ለእግዚአብሔር...............89
44) ትዕቢተኛው ዝኆን.......................92
45) ዝናብና ጽጌረዳ.............................95
46) የሾላውና የዱባ ፍሬ......................97
47) የሚሊዮን ዶላር መድህን.............99
48) አቧራን ማራገፍ.........................102
49) ወንዙን መሰማመጥ...................104
50) ማነው ባለጠጋ?.........................106
51) የረዳት ያሰህ! .........................107
እንሰናበት........................................................110


## መነሻ ነጥቦች

በየዕለቱም ባይሆን ዕረፍት ሲኖረኝ ከርብቃና ኢፍሬም ጋር አራት የምበላው ፍቅር ካፌ ውስጥ ነው። ሁሌም የሚቀርብልን ምግብ በባለሙያ የተከሸነ መሆኑን ሃሳታችንም በአንድ ድምፅ አንሰማማበታሰን። ይህንን እኛ ብቻ ሳንሆን ሌሎችም እንግዶች ደጋግመው በዓመታት መካከል የመሰከሩት ነው። በልተን ስንጨርስ አንድም ቀን የሒሳብ መጠየቂያ ወረቀት አልቀረበልንም። የሰጠንን ፈጣሪ አመስግነን እንደምንበላ ሁሉ የሠሩና የሰጡንን ጣቶችም ባርከን ነው የምንነሣው። ፍቅር ካፌ ውስጥ መመገብ የምናዘወትርባቸው ምክንያቶች ግን እነዚህ አይደሉም። ካፌው እኛ ቤት ውስጥ ስለሆነ እንጂ።

የካፌው ዋና ሥራ አስኪያጅ ደግሞ የኔ ባለቤትና የልጆቼ እናት ፍቅር ናት። የ አርስዋ ምግብ ቤት ውጭ የመብላት ፍላጎታችንን አዳክሞ የአቅርቦቱን መልክ እየቀያየረ ላለፉት አስራ አንድ ዓመታት አገልግሎቱን ቀጥሏል። በዓመት ውስጥ ዐቅደን፣ ወጥተንና ከፍለን የምንበላባቸው ቀኖች በጣት ይቆጠራሉ። በዚህ አጋጣሚም ለእኔ ለአዘጋጁና ለሁለቱ ልጆቼ ስለሚደረግልን እንክብካቤ ሁሉ የኩሽናዋን እመቤት ላመስግናት አወዳለሁ።

ፍቅር ካፌ ውስጥ በሚኖረን አጭር ቆይታ የገበታ ላይ ወጎች ለቤታችን አዲስ አይደሉም። ገና ለአራት

ስንታደም ልጆቼ "ዳዲ ስቶሪ ንገረን" ይሉኛል። አባባላቸውን ቃል በቃል ነው ያስቀመጥኩት። እኔም ትዝ ያለኝን እንደ አመቺነቱ በእንቅስቃሴ እያጀብኩ አወራላቸውና አስከትዬ ከታሪኩ ምን እንደምንማር እጠይቃቸዋለሁ። ምክንያቱም ዋነኛው ዓላማዬ እነርሱን በተረት ተረት ማዝናናት ሳይሆን አጋጣሚውን ተጠቅሜ ዘመን የማይሽረውን ሰማያዊ እውነት ማካፈል ነው። እነርሱም እጅ ከማውጣት አልፈው "እኔ እኔ" ብለው እየተሽቀዳደሙ የገባቸውን ይመልሳሉ። ያንን ተከትዬ በበኩሌ እንደገባኝ ማጠቃለያውንና ዋናውን መልእክት አስተላልፋለሁ።

በጣት ለሚቆጠሩ ጊዜያት ደግሞ ልጆቼ ውለታዬን ለመክፈልም ይሁን ለልምምድ የ እነርሱን ታሪኮች ነግረውኛል። "ዶሮዋ በከተማ" እና "ማነው ባለጢጋ" የሚሉት በዚህች ጥራዝ ውስጥ ለናሙናነት የተጨመሩት የኤፍሬምና ርብቃ ትረካዎች ፈጽሞ የምዘነጋቸው አይደሉም። ኤፍሬም ከቅዳሜ ትምህርት ቤት ያገኘው ሲሆን ርብቃ ግን ፈጥራ ነው ያጫወተችን።

ባለቤቴ ፍቅር ግን ከእኛ ጋር ቁጭ ብላ ከመመገብ ይልቅ እኛን ማገልገሉ ስለሚያስደስታት ወደ ኩሽናዋ ገባ ወጣ ትላለች። ማለቂያ የሌለውን የማንኪያ ሹካ ጥያቄ ያለድካም ታስተናግዳለች። እናም ብዙ አትሰማንም። ለጥቂት ጊዜያት እንዲሁ እንደተጓዝን ቀስ በቀስ በጨዋታችን መሳብ ጀመረች። ያልተሰማትን እንድንደግም እየጠየቀችም



ማዳመጥ ለመደች። ብዙም ሳትቆይ አንድ ቀን የዕለቱን ታሪክ እንደጨረሰን እነዚህን ወሬዎች እየጻፍኳቸው እንደሆነ ጠየቀችኝ። እኔም እንዳልጻፍኳቸው ያንንም ለማድረግ እንዳላሰብኩ ይልቁንም ብዙ የሚጻፉ ሌሎች ነገሮች እንዳሉኝ አብራራሁላት። እርሷ ግን ፍንክችም አላለች። "እነዚህን የመሰሉ ታሪኮች ይልቁንም ከዕለታዊ ኑሮአችን ጋር ያላቸው ተዛምዶና ያዘሉት ትምህርት ሊጻፍ እንደሚገባ አምናለሁ። አደራህን የትም እንዳትበትናቸው!" ስትል አሳሳበችኝ። እንደማስብበት ነግሬያት ተለያየን። መጀመሪያ ሰሞን ብዙም አላተኮርኩበትም። እየቆየ ሲሄድ ግን ያለችውን አመንኩበት። እናም ሲመቸኝ እመለሰባቸዋለሁ እልኩና ማስታወሻ ላይ ርዕሶቹን ብቻ ማስቀመጥ ጀመርኩ። ጊዜው ሲደርስም እነሆ የማስታውሳቸውን እምሳ ያህሉን አሰፈርኩ።

እኛም እንደ ሌሎቹ ታሪክ መፍጠር እንደምንችል ለማሳየት ከጨመርኳት ተነጥላ የሄደችው በግ ከሚለው የራሴ ፈጠራ ታሪክ በስተቀር ብዙዎቹ ከንባብ፣ ከእፊ ታሪክና በሰሚ ሰሚ የተገኙ ሕዝባዊ ታሪኮች ናቸው። ስለዚህ ለገበታ ወግ ከመጠቀም ባለፈ ጥብቅና ልንቆምላቸው አይቻለንም። የቅጂ መብት ጉዳይ ቢነሣ እንኳ የትርጓሜዎቹ እንጂ የታሪኮቹ ሊሆን ከቶም አይችልም። ስለዚህ ያለመከልከል ልንነጋገርባቸው እንችላለን ማለት ነው።

ምድራዊውን ተረት በሰማያዊው ቅኝት እንዴ፡ መመልከት እንደሚቻል ይህች መጽሐፍ መጠነኛ ጥቆ ልትሰጥ ትችላለች። ያችን ፍንጭ ይዞ ማስፋት ደግ የአንባቢው እ ስደሳች ኃላፊነት ይሆናል። ከዚህ እንጻ ታሪኮቹ በቤተሰብ መካከል ለየት ያለ ንግግር ለማስጀመ ሊያግዙ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ። በተለይ ከምድራች ርቀን ለምንኖረው ለ እኛ ልጆቻችን የአገራችንን ትውፊት እንዲያውቁና ባሕ ላችንንም እንዲረዱ በር ይከፍቱላቸዋል። በአንድ ገበታ የሚበላው ቤተሰብም ጆሮ ላይ ከሚሰካ የራስ ዓለም ወጥቶ አንድ መሆን እንዲችል ያበረታታሉ። ዐይንን ከማያቋርጠው የቴሌቪዥን ጎርፍ ጆሮንም ከሙዚቃው ፋንፋር ያሳርፋሉ። የተረው ታሪኮችን ለማስታወስና የራስንም ለመፍጠር ያነሳሳሉ። ልጆችም የንግግርን ጥበብ ገና ከአፍላ ዕድሜአቸው እንዲማሩ የመጀመሪያውን አስደሳች መድረክ ያመቻቻሉ። ፈንጠር ሲልም ታሪኮቹ ይልቁንም ከነርሱ የሚገበዩት ትምህርቶችና የተመረጡላቸው ጥቅሶች ለሰባኪዎች፣ አስተማሪዎችና ጸሐ ፍት በመነሻ አሳብነት ብሎም በማሳያነት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

ፍቅር ካሬ ውስጥ ወደሚገኘው የቤተሰባችን ገበታ እንኳን ደህና መጡ!

መልካም ንባብ......

ኤፍሬም፣ ርብቃ ዓለማየሁና ፍቅር።

አስፐን ሒል (ሜሪላንድ ክፍለ ግዛት) አሜሪካ



## ምስጋና መልካም ነው!

“ማየት የተሳነኝ ነኝ፡ እባካችሁ እርዱኝ” የሚል ጽሑፍ ከፊት ለፊቱ አስቀምጦና የምፅዋት መጣያ ባርኔጣ ደቅኖ ይለምናል ታዳጊው ወጣት። እናም አልፎ አልፎ ጥቂት ሳንቲሞች ቅጭል ሲሉለት ቆየ። ረፋዱ ላይ አንድ መንገደኛ እንደ ሌሎች ምፅዋት መወርወር ብቻ ሳይሆን ጽሑፉንም ቀይሮት ሄደ። ብዙም ሳይቆይ ባርኔጣው በሳንቲሞች ሞልቶ ተረፈ።

ከሰዓት በኋላ ያ ሰው ውጤቱን ለማየት ተመልሶ መጣ። ለማኙም በኮቴው ለየውና “ጠዋት ጽሑፌን የቀየርከው አንተ ነህ አይደል? ምን ብለህ ጻፍክ ለመሆኑ?” የሚል ጥያቄ አቀረበለት። “እይ አንተው ያልከውን ነው የደገምኩት፤ ግን በተለየ መንገድ እንዲህ ብዬ አቀረብኩት፤ ዛሬ ውብ ቀን ነው፤ እኔ ግን አላየውም! አየህ የመጀመሪያው ያንተን አለማየት ብቻ ነው የሚናገር። ሁለተኛው ግን ማየት መቻል መታደል መሆኑን ለሌሎች ያስታውሳል፤ ያኔ ምስጋናቸውን ምፅዋት በመስጠት ይገልጣሉ ”።

### ምን ያስተምረናል?

ይህ አስተዋይ ሰው አላፊ አግዳሚውን ለምስጋና አነሳሳቷል። ማየት የሚችሉትን ሁሉ የብርሃን አምላክ የዐይናቸውም ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን

እንዲያስታውሱ ረድቷል። ያኔ እንደ እነርሱ ለማየት ያልታደለውን ወ ጣት በምፅዋት ለመባረክ አላመነቱም። በዚህ ዘመን ያለን እኛም እንደዚያ ሰው ዓለሙ ሁሉ የእግዚአብሔርን መልካምነት እንዲያስታውስ አንድ ነገር ማድረግ ያስፈልገናል!

## መጀመሪያ መቀመጫዬን

መንገደኛው ጥቅጥቅ ባለ ዱር ውስጥ እያሳበረ ሳለ አንድ ዝንጀሮ በርቀት ይመለከታል። እየቀረበ ሲሄድም ከእግር እስከራሷ በእሾህ መወረሷን አስተዋለ። እናም ሁኔታዋ ስላሳዘነው ተጠግቶ እንዲህ አላት። "ልረዳሽ እፈልጋለሁ፤ ግን ስለ ምቸኩል ይህንን እገር ሙሉ እሾህ ልነቅልልሽ አልችልም። ስለዚህ የትኛውን የሰውነትሽን ክፍል ቶሎ ነቅዬልሽ ልሂድ።"

እርስዋም ሳታመነታ እንዲህ መለሰች። "መቀመጫዬ ላይ የተሰገሰገውን ንቀልልኝ። ምክንያቱም መቀመጥ ከቻልኩ የቀረውን እኔው ቀስ እያልኩ ነቅዬ እጨርሰዋለሁ።"

### ምን ያስተምረናል?

መቀመጥ ከቻልኩ የቀረውን መንቀል እያቅተኝም የሚለው እስተሳሰብ ጥልቅ ነው። የተከበብነው መቀመጥ ባልቻለ ትውልድ ነ ውና። ሰው ለመስማት የሚችለው



ሲቀመጥ ነው። በቅጡ ማሰብ ወይም በትክክል ማቀድ የሚችለውም አረፍ ብሎ ነው። እየሮጡ መመካከር አይሞከርም። መቀመጥ ወይም በመንፈሳዊው አባባል ማረፍ የመታመን ምልክት እንደሆነም መዘንጋት የለብንም። "የሚሰማኝ ግን በርጋታ ይቀመጣል፤ ከመከራም ስጋት ያርፋል" ምሳ.1:33።

## ሰላምህን ያዝ

ጎረቤታሞች ቢሆኑም የኑሮ ደረጃቸው ግን ለየቅል ነበር። አንዱ መናጢ ድሃ ሌላው የለየለት ሃብታም። ታዲያ ድሃው ማንጎራጎር ይወድ ነበር። የሚያማልል ድምፅ ም ነበረው። ከዚህ የተነሳ ሃብታሙ የእርሱን እንጉርጉሮዎች ላይሰማ መዋል አይሆንለትም። ይህ ለዓመታት ከቀጠለ በኋላ ባለሃብቱ ለዚህ ሰው አንድ ስጦታ ላበረከትለት ይገባል የሚል ውሳኔ ላይ ይደርሳል። እናም አስጠርቶ አንድ ከረጢት ወርቅ ይሸልመዋል። ድሃው በዚህ እጅግ ቢደሰትም ስጋትንም አብሮ ተቀበለ። ስለዚህም ቶሎ ወጥቶ ከጓሮው ቈፈረና ወርቁን ቀበረው። ያም ብዙ አልረዳውም።

ወርቅ መቀበሌን ምናልባት የሰማ፣
ሌባስ ቢመጣብኝ ገድሎ የሚቀማ።

እያለ በእሳብ ለመወጠር ብዙም ጊዜ አልወሰደበትም። እንቅልፍ የለሽ ሌሊቶችን ማሳለፍ ጀመረ። ከዚያች ቀን ጀምሮ ድምፁን እንሥቶ አላንጎራጎረም። ከአያሌ ቀናት በኋላ ግን አንድ ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ ደረሰ። ከአንድ ከረጢት ወርቅ ይልቅ ለላምና ደስታው እንደሚበልጥ አመነ። እናም በማለዳ ገሥግሦ ሄደና ወርቁን ለባለጠጋው መለሰለት።

## ምን ያስተምረናል?

ምንም ዓይነት ንብረት ከውስጣዊ ሰላማችን አይበልጥም። አንድ የዐዋቂዎች አባባል አለ። "ገንዘብ ቤትን ሊገዛ ይችላል፤ ቤተሰብን ግን አይደለም። አልጋን ሊገዛ ይችላል፤ እንቅልፍን ግን አይደለም። ምግብን ሊገዛ ይችላል፤ የመብላት ፍላጎትን ግን አይደለም " ይላል። እናም ለመበልጠግ ብለን ለላማችንን ለጊዜአዊ ጥቅም ብለን ዘላለማችንን ማስወሰድ ሞኝነት ነው። "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ" ሮሜ.5:1።

## የስልት ቅያሪ

እንበሳ ከልክ በላይ ተርቦ በጫካ ውስጥ እየተጓዘ ሳለ "ዛሬ ምንም ዓይነት እንስሳ ባገኝ እበላለሁ" ሲል ለራሱ ቃል



ያገባል። ብዙም ሳይሄድ ታዲያ ጦጢትን ያገኛታል። ገና ከሩቁ ስታየው ያለበት ሁኔታ ገብቷት ስለነበር ዘልላ ዛፍ ላይ ትወጣለች። እንበሳም በጓደኛነት ሊያናግራት ይጀምራል።

"ጦጢት አንድ የምነግርሽ ምሥጢር ነበረኝ "

"ንገረኛ አያ እንበሶ"

"ምሥጢርማ በአደባባይ አይደለም፤ በጆሮሽ ነው የምነግርሽ"

"እኔ ከዚህ አልወርድም፤ ትነግረኝ እንደሆነ ንገረኝ፡ ያለበለዚያ ተወው!"

"ምን አስፈራሽ ጦጢት፤ እኔኮ አልበላሽም"

"አልበላሽምን ምን አመጣው ታዲያ?"

## ምን ያስተምረናል?

የባላጋራችን የተለሳለሰ አቀራረብ እንዳያዘናጋን ነው። ቅዱሱ መጽሐፍ "በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ እንበሳ ይዞራልና" ይላል (1ጴጥ.5:8)። ጠላታችን ዲያብሎስ ክፉ ነው። ሊያጠፋ ሊያርድ እና ሊገድል እንጂ አንድም ቀን ራርቶ ሊረዳን አይመጣም። በርግጥም ጠላታችን ያለማቋረጥ ስልቱን ይለዋውጣል፤ በቃሉ ላስታጠቀን ልዑል እግዚአብሔር ክብር ይሁንና እኛ ግን አንስተውም!

## ሰው ለሰው

ግለሰቡ በጠና ከታመመ ይልቁንም የአልጋ ቁራኛ ከሆነ ለነበተ። ከዛሬ ነገ ይሞታል ተብሎ ሲጠበቅ ባልታሰበ አኳኋን የከፍተኛው ሎተሪ ባለ ልዩ ዕጣ አሸናፊ ሆነ። ይህኔ ቤተሰቦቹ የሚያደርጉት ጠፋቸው። ለምን ቢሉ ይህንን አስደሳች ወሬ እንዴት እንደሚነግሩት ተቸግረው ነው። ማሸነፉን የማወቅ መብት እንዳለው ተስማምተዋል። ግን የቸገራቸው ሲሰማ ምን ይሆናል የሚለው መላምት ብቻ ነው። በጣም ተደሰቶ ከአልጋው ሊነሣ ይችላል። ይህ መልካም ነገር ነው። ግን በድንጋጤ ልቡ ቀጥ ብትልስ?

ለማንኛውም ባለሙያው መላ አያጣም እሉና ተመላልሶ ለሚያከመው ዶክተር ነገሩን አማከሩት። እርሱም "ይህ አስደሳች ዜና ነው፤ እኔው እያዋዛሁ እነግረዋለሁ" በማለት ነገሩን አቀለለላቸው። በዚሁ መሠረት ከበሽተኛው ጋር ስለውሎውና ስለአዳሩ ሲጫወቱ ቆዩ። በመሃሉ ሐኪሙ "ለመሆኑ አሁን አንድ ሚሊዮን ዶላር በሎተሪ ቢደርስህ ምን ታደርግበታለህ?" ብሎ ይጠይቃል። በሽተኛውም ዘና ብሎ "ምን እንደማደርግበት አላውቅም፤ ግን ባለውለታዬ ነህና ያለጥርጥር ግማሹን ለአንተ እሰጥህ ነበር" ሲል መለሰ። ይህኔ ዶክተሩ በድንገተኛ የልብ ድካም አሸለበ።

ምን ያስተምረናል?



የሰዎችን ዕውቀት አንንቅም። ግን በሁሉ ነገር በሥጋ ለባሽ መታመን አይቻልም። ዶክተርም ይሁን ፕሮፌሰር ራሱ ተሰባሪ ነው። አቅሙም ውሱን ነው። አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ የሚል ድንጋጌ ለሁሉ ተሰጥቷል። የዕውቀት ጥግ ደርሷል የምንለው ሰው አንድ ቦታ ሲደርስ ማጣፊያው ያጥረዋል። ስለዚህም ሲመከረን ዘመን የማይሽረው የአምላካችን ቃል እንዲህ ይለናል። " እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ጠቢብ በጥበቡ አይመካ፥ ኃያልም በኃይሉ አይመካ፥ ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ፤ ነገር ግን የሚመካው። ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ በዚህ ይመካ፤ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና፥ ይላል እግዚአብሔር" (ኤር.9፡23-24)።

## እረኛውን ማወቅ

ብዙ ሰባኪዎች ምዕመኑን ማሳተፍ ይወዳሉ። ለዚህም ይመስላል "እጠገብህ ላለው እንዲህ በለው፤ አሜን በሉ እንጂ" ወዘተ...የሚሉት።

ታዲያ አንድ ቀን አንዱ መጋቢ መዝሙር ሃያ አራትን በቃሉ የሚያውቅ ሰው ካለ ተነሥቶ በቃሉ እንዲወርደው ይጠይቃል። ለዚህም አንድ ወጣትና አንድ

ሽማግሌ እጃቸውን ያነሣሉ። መጀመሪያ ዕድሉን ያገኘው ወጣት "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም" ብሎ ይጀምርና እንደ ጥይት በመወንጨፍ ላስ ያደርጋታል። በዚህም ጉባዔው በብዙ እድናቆት ተሞላ። ሽማግሌው ግን እየተደናቀፉና አንዳንዴም እየደገሙ በቀሰስተኛ ድምፅ ነበር መዝሙሩን የወጡት። ሲጨርሱ ጉባኤተኞቹ በሙሉ እንባ አቅርረው ነበር። እናም መጋቢው ወደ ስብከቱ ከመመለሱ በፊት የተፈጠረውን ነገር እንዲህ ሲል ገምግሞታል። "ወጣቱ መዝሙሩን ጠንቅቆ ያውቀዋል፤ እሳቸው ግን ራሱን እረኛውን ያውቁታል!"

## ምን ያስተምረናል?

ስለ እግዚአብሔር ማወቅና እግዚአብሔርን ማወቅ የሰማይና ምድርን ያህል የተራራቁ ሁለት ነገሮች ናቸው። በምድራችን ላይ እግዚአብሔርን እናውቅም ወይም መኖሩን እናምንም የሚሉ ሰዎች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ግን እናውቃለን ከሚሉት መካከል አብዛኞቹ እንደዚህ ወጣት ናቸው። ቃሉን ያውቃሉ፤ እረኛውን ግን አያውቁትም። በሌላ አነጋገር የሚገባውን እውቅና አይሰጡትም። " ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ



ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።" (ማቴ.7:24-27)።

# ከዶሮች ጋር የዋለው ንስር

አንድ እረኛ በጫካ ውስጥ ሲዘዋወር የንስር እንቁላል ያገኛል። አምጥቶም ለእናቱ ይሰጣታል። እርሷም በተራዋ ከሌሎች ጋር ቀላቅላ ጭር ላለችው ዶሮ ታስታቅፋታለች። ጊዜውን ጠብቆ ንስሩም ከጫጩቶች ጋር ይፈለፈላል። አብሮም መሬት መጫር ይጀምራል።

ግን ንስሩ ከሌሎች የሚለይበት አንድ ባሕርይ ነበረው። ሌሎቹ በትጋት መሬት ሲጭሩ እርሱ ግን አያቋረጠ ቀና ይላል። በሰማይ የሚበሩትን እዕዋፍም ትክ ብሎ ይመለከታል። እንደ እነርሱ የመብረር ፍላጎት ነበረውና። ሌሎቹ ዶሮች ደግሞ "እርፈህ መሬትህን ጫር፤ እነዚያ ንስሮች ናቸው። አንተ ግን ዶሮ ነህ" እያሉ ያላግጡበት ነበር። እናም ማንም ሳይረዳው እንዲሁ መብረር እንደተመኘና መሬት እንደጫረ አለፈ።

## ምን ያስተምረናል?

ሕልምን ለአሳጋጮች መንገር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የዮሴፍ ወንድሞች "ሕልመኛው መጣ"

የተባባሉት ስለሕልም ስለማያውቁ ሳይሆን ታላቆቹ እያ( እርሱ የሚያልምበት እውነት ስላልተዋጠላቸው ነው። ዛሬያ እነርሱን የሚመስሉ ሰዎች በዙሪያችን ተኮልኩለዋል፡ በምክር ሰበብ ራዕይን ከሚገድሉ ሰዎች መራቅ የማንም ሳይሆን የባለራዕዩ ኃላፊነት ነው። ይይልቁንም እነእኛ ከማያምኑት ጋር  የሚኖረን ሕብረት ብዙ ማስተዋልና ጥንቃቄ የሚያሻው ነው። "ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? "(2 ቆሮ.6: 14-16)።

## ይቅርታን እንምረጥ

ጆርጅ ዊልሰንና ጀምስ ፖርተር በነሐሴ 6 1829 (እ.አ.አ) የፈጸሙትን ወንጀል ተከትሎ በስቅላት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው ። ጀምስ ፖርተር በተቀጠረው ቀን ተሰቀለ። ጆርጅ ዊልሰን ግን እንደ አጋጣሚ በዚያ ቀን የተደገሰለትን የሞት ፍርድ አመለጠ። ይህንኑ ተከትለው ደግሞ ወዳጆቹ ምሕረት ይደረግለት ዘንድ በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት



ለነበሩት አንድሩ ጃክሰን አቤት አሉ። ፕሬዚዳንቱም በዚሁ ተስማሙ። እናም ጆርጅ ዊልሰን መሞቱ ቀርቶ በሃያ ዓመታት እሥራት እንዲቀጣ ፍርዱን አሻሻሉለት። ዊልሰን ግን "ይቅርታውን አልቀበልም" በማለት ተቃወመ። ማንም በግድ ይቅርታ ላድርግልህ ሊለኝ አይችልም ሲልም ፍርድ ቤት ቀረበ።

ጉዳዩ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ እንደ ደረሰ ዐቃቤ ሕጉ ተከታዩን አስተያየት አሰፈረበት ። "አስረኛው ፈቅዶ እስካልተቀበለው ድረስ ፍርድ ቤቱ ማንንም ይቅርታን ተቀበል ብሎ  የማስገደድ መብት የለውም ። ይቅርታ ተደርጎለታል፤ ግን መቀበል ወይም አለመቀበል የግለሰቡ ጉዳይ ነው። ደስ ያለውን የመምረጥ መብቱ አይሸራረፍም።"

ዋናው ዳኛ  ጆን ማርሻል በበኩላቸው የሚከተለውን መደምደሚያ በማከል ዊልሰን የዳዳለትን የሞት ፍርድ አጸደቁለት ። "ምሕረት ሕጋዊ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የሚመነጭ በጎ ስጦታ ነው። ማንኛውንም ተከሳሽ ከወንጀሉ የተነሣ ከሚያገኘው ቅጣት ይታደገዋል ። ግን  ለተቀባዩ እስካልደረሰና እርሱም በእሺታ እስካልተቀበለው ድረስ የተሟላ አይሆንም። ግለሰቡ አልቀበለውም ካለ ደግሞ እርሱን የምናስገድድበት ምንም ኃይል የለንም ። ሞት የተፈረደበት ሰው እንዴት ምሕረትን ይቃወማል ብለን ማሰቡ ቢከብድም ቅሉ ምሕረት ግን ለነፍስ ገዳይም ይሁን

ለተራ ጥፋተኛ የሚሠራው በተመሳሳይ አገባብ ነው ። እናያ ጆርጅ ዊልሰን መሰቀል አለበት!"

### ምን ያስተምረናል?

ጆርጅ ዊልሰን ይቅርታ የሌለው ኃጢአት ፈጸመ። ጥፋቱ ይቅርታ ያጣው ግን ሰው የመግደል ወንጀል በመፈጸሙ ሣይሆን ይቅርታን ሊቀበል ባለመፍቀዱ ነው። በዚህም ከምሕረት ይልቅ ሞትን መረጠ! ተሰቀለ! ምን ዓይነት ጅልነት ነው? ግን ከእርሱም የባሰ አሳዛኝ ምርጫ እያደረጉ ወደጥፋት የሚጓዙ ሰዎች ቁጥር ብዙ እጅግ ብዙ ነው። እኛ ግን ቀሪውን ዘመን ይልቁንም የዘላለምን ሕይወት ስናስብ የዊልሰንን ስሕተት እንድገም! ይቅርታን እንምረጥ! " በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።" (ዮሐ.3:16-18)።

## ስፍራህን አትልቀቅ

ስለ አንድ አፍሪካዊ ገበሬ የሚነገር አሳዛኝና ልብ የሚነካ ታሪክ አለ ። ገበሬው ከትውልድ ወደ ትውልድ



በውርስ የተሸጋገረ ሰፊ የእርሻ መሬት ነበረው። ሆኖም በእርሱ ዘመን በግብርና መኖር ከማይችልበት ሁኔታ ላይ ያደረሱት ሁለት ነገሮች ተፈጠሩ። የመጀመሪያው በቀላሉ ከብልጥግና ጣሪያ ላይ የሚደረስበት የዕንቁ ንግድ ወሬ ነው። ሁለተኛው ደግሞ አድካሚው የእርሻ ሥራ አንገፈገፈው። ስለዚህም ትልቁን የእርሻ መሬት ሸጦ በዕንቁ ፍለጋ ሥራ ላይ ተሰማራ።

ግን እንደተወራው አልተሳካለትም። ለዓመታት ከተንከራተተና ጥሪቱን ከጨረሰ በኋላ ከድህነት አዘቅት ዉስጥ ወደቀ። ስለሆነም ወደ ትውልድ መንደሩ ተመልሶ የራሱን እርሻ ለገዙት ሰዎች ተቀጠረ። ከዕለታት በአንዱ ቀን በእርሻው መሃል ሊጓዝ ድንጋይ ያደናቅፈዋል። ጎንበስ ብሎ ሲመለከተው ግን ድንጋዩ ተራ አልነበረም። ከዚያ ቀደም ተገኝቶ የማያውቅ ትልቅ ዕንቁ እንጂ!

### ምን ያስተምረናል?

ያለምሪት ሥፍራን መልቀቅ ኪሣራ አለው። የሩት መጽሐፍ እንደሚነገረን ኑኃሚን በዚህ አልፋለች። ወደባዕድ ምድር መሰደዷ ባልና ልጆቿን ከማጣት ሌላ የፈየደላት ነገር አልነበረም። የጊዜውን ረሃብ ተቋቁመው በቦታቸው ለቆዩት ግን የመኅበኘት ዘመናቸው ቀረበ (ሩት.1:6)። ኑኃሚን ይህንን ለምታ ወደ አገሯ ተመለሰች። ገበሬው ወሬ ብቻ ሰምቶ እርሻውን ሸጦ ዕንቁ ፍለጋ ቢሄድም ዕንቁው ግን

የነበረው ከአግሩ በታች ነበር። ዛሬም በባዕድ ምድር ስኬትን ፍለጋ የሞቀ ትዳራቸውን የተከበሩበትን ሥራ ወዳጅና ዘመድን በትነው የሚሰደዱ ቁጥር በሚሊዮኖች ነው። በፀፀትም ዕድሜያቸውን ይገፋሉ!

## አባቴ ገመዱን ይያዝ!

በአንድ የገጠር ቀበሌ በመጥፋት ላይ ያሉ ዕፅዋትን ፍለጋ የተሰማሩ ጥቂት የ መስኩ ተመራማሪዎች ነበሩ። ከሰዓታት ዙረት በኋላ አንድ አሰደናቂ ግኝት ይጨብጣሉ። ይኸውም ከምድረ ገጽ እንደጠፉች የሚገመት ቆንጆ የአበባ ተክል ማግኘታቸው ነበር። ግን ብዙም ሳይቆዩ ሌላ ችግር አብሮ መከሰቱን ተገነዘቡ። አበባዋ የበቀለችው በሰምጥ ሸለቆ ዉስጥ ለዚያውም ወገቡ ላይ ነበር። ከብዙ ውይይትና ግምገማ በኋላ ያላቸው ዕድል አንድ ብቻ እንደሆነ ተስማሙ። ይኸውም ከብደቱ ቀለል ያለ ሰው ፈልጎ ወገቡን በገመድ ማሰርና አበባዋን እንዲያመጣ ወደታች መልቀቅ ነበር።

በዚያም መሠረት በአካባቢው ከብቶችን የሚጠብቅ ወጣት አግኝተው አግባቡት። ለ ወሮታውም ጠቀም ያለ ገንዘብ ሊሰጡት ተስማሙ። ልጁም በቀረበለት ጥያቄና በሽልማቱ ተስማምቶ ወደ ጉድጓዱ ከመግባቱ በፊት ቤቱ ደርሶ ለመምጣት ጠየቀ። አያቅማሙ ፈቀዱለት።



ይመለሳልም ብለው አልገመቱም። አረኛው ግን ብዙም ሳይቆይ አንድ ሰው አስከትሎ ከተፍ አለ። አናም ለተመራማሪዎቹ እንዲህ አላቸው። "አሁን ዝግጁ ነኝ፤ የምገባው ግን በአንድ ቅድመ ሁኔታ ከተስማማችሁ ነው፡ የምታሰርበትን ገመድ ጫፍ እንዲይዝ የምፈልገውን ሰው አምጥቻለሁ፤ አርሱም አባቴ ነው!"

### ምን ያስተምረናል?

ልጁ ለዚህ ፈታኝ ሥራ ዝግጁ ቢሆንም ገመዱ ግን በባዕዳን እንዲያዝ አልፈቀደም። ለምን ቢሉ ነፍሱ በገመዱ ጫፍ እንደምትንጠለጠል ያውቃል። ስለ አርሱ ሕይወ ት ደግሞ ከአባቱ የበለጠ ተቆርቋሪ የለም። ወዳጄ ሆይ የሕይወትህን ገመድ ብቻ ሳይሆን አስትንፋስህንም ጭምር የያዘውን ጌታ አባቴ ስትለው ድፍረትህ ይጨምራል። ምትንም ትንቀዋለህ። ታላላቅ ሥራዎችን አከናውነህ ለማለፍ በሩ ወለል ብሎ ይከፈትልሃል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከተወልን ጉልህ ምሳሌዎች አንዱ ነፍሱን ለአምላኩ አደራ መስጠቱ ነው። "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ አሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ" ሉቃ.23:46።

## ዶሮዋ በከተማ ተራኪ ኤፍሬም ዓለማየሁ

ሉሉ የተባለች ዶሮ በአርሻው አካባቢ ትኖር ነበር ግን የገጠሩ ኑሮ እየጎመዘዛት ሄደ። በየዕለቱ የምታያቸው ነገሮች የምትሄድባቸው ቦታዎች ሁሌም ያው መሆናቸው ብሎም መደጋገማቸው ሰለቻት።

"አዲስ ነገር ያስፈልገኛል" አለች ሉሉ ለራስዋ። "ወ. ከተማ እሄዳለሁ፤ ማድረግ ያለብኝም ይህንኑ ነው "።

በአንድ የፀደይ ቀን ሻ ንጣዋን ሸከፋ ከንፎቿ በማራገብ ተሰናብታ ነጎደች።

በከተማ ሉሉ የሚያጓጉ አዳዲስ ነገሮችን አየች። ረግጣቸው የማታውቀውን በርካታ ቦታዎች ጎበኘች። ብዙ አዳዲስ ሰዎችና እንስሳትንም ተመለከተች። ስሜቶቿም ተቀያየሩ። ካየቻቸው አስደናቂ ነገሮች የተነሣ በሐሤት፣ መደነቅ፣ መገረምና መደመም ተሞላች። ያልጠበቀችው ሌላም ዓይነት አዲስ ስሜት ሞልቷት ነበር። ብቸኝነት!

በአርሻዋ ላይ የተወቻቸው ጓደኞቿ ናፈቋት። ይህኔ የከተማው ኑሮ ለዛው እየተሟጠጠ ሄደ። "እኔ በልቤ የገጠር ዶሮ ነኝ "አለች ሉሉ ከተማውን ለመልቀቅ ስታኮበኩብ።

እንደገና ሻንጣዋን ሸከፋ በሚቀጥለው አውቶቡስ ወደ ቤትዋ ተመለሰች። ብቻዋን ሌላ ቀን ከማሳለፏ በፊት።

በአርሻው የሉሉ ጓደኞች ትልቅ ፌስታ አካሄዱ። "እንኳን በደህና ተመለስሽ ሉሉ" የሚል ቅስት ሰቅለው ያለማመንታት እንደገና ተቀበሏት። ሉሉ የቀደሙ ወዳጆቿን፣ የቀደሙትን ቦታዎችና የቀደሙትን ነገሮች ስታይ ደስ አላት።



በዚያ ምሽት በጎጆዋ ውስጥ ለራስዋ እንዲህ አለች። "አዲስ ነገር ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ የቀደመው ግን በጣም ጥሩ ነው"።

## ምን ያስተምረናል?

አዲስ ነገር ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ዘመናቸውን የሚጨርሱ ጥቂት አይደሉም። ግን አዲስ የሚመስለው ሁሉ አዲስ አይደለም። ወይም ሲጨበጥ ባዶ ሊሆን ይችላል። በርግጥም ዐዋቂዎች እንደሚሉት የሚያብለጨልጨው ሁሉ ወርቅ አይደለም። በተለይ የሚያምን ሰው ረግቶ መጭውን ነገር ከጌታ መቀበል አለበት። ያለበለዚያ በግሣንግሡ ይረታና ሕይወቱን ይጥላል። በዴማስ ሕይወት የሆነው ይህ ነው። "ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና፥ ወደ ተሰሎንቄም ሄዶአል" 2 ጢሞ. 4:10።

## ይሰጣል እንጂ አይሸጥም

ልጇ የታመመችባት እናት ወደ ቤተ መንግሥቱ ታቀናለች። ልጇ አማረኝ ያለቻት የበሰለ የወይን ፍሬ ያለው እዚያ ግቢ መሆኑን ሰምታ ነበርና። እናም የንጉሡን ሴት ልጅ አግኝታ ችግሯን ታዋያታለች። እሷም ያለምንም ማቅማማት ወደ ውስጥ ዘልቃ የተንዠረገገውን ወይን አምጥታ ትሰጣታለች። እናትም በበኩሏ እጅ ነስታና

አመስግና ያላትን ትዘረጋለች። ለመከፈል መሆኑ ነው። የንጉሡ ሴት ልጅ ግን አልተቀበለቻትም። ግን እንዲህ አለቻት። "አባቴ ይሰጣል እንጂ አይሸጥም"።

## ምን ያስተምረናል?

ንጉሡ የተረፈው ስለሆነ በወይን ፍሬ ቸርቻሮ አይኖርም። ያንን ለማድረግም ከ ብሩ አይፈቅድለትም። ስለዚህ ነው ልጅቱ በሙሉ ድፍረት "አባቴ ይሰጣል እንጂ አይሸጥም" ማለቷ።

ዘላለማዊው ንጉሥም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ባሕርይ አለው። ሁሉን በነፃ ይሰጣል እንጂ አይሸጥም። ለጋስ ነው። ቸር ነው። ርኅሩኅ ነው። በመስጠት ደስ ይለዋል። ለመሆኑ የዘላለም ሕይወት ዋጋ ስንት ትሪሊዮን ዶላር ነው? ማንስ ችሎ ይገዛዋል? ክብር ለሰማያዊው ንጉሥ ይሁንና ያንን የሞት መድኃኒት እንዲሁ በነፃ ሰጥቶናል! "መንፈሱና ሙሽራይቱም። ና ይላሉ። የሚሰማም። ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ" ራዕ.22:17።

# የባሰ አለና

አንድ ኑሮ ያማረረው ሰው ችግሩን ለማዋየት በአካባቢው ወዳለ ጥበበኛ ይሄዳል። እንዲህም ይለዋል።"



እስቸኳይ እርዳታ እፈልጋለሁ። ያለበለዚያ ማበዴ ነው። እኔ፤ ባለቤቴ፤ ልጆቼና አማቾቼ በአንዲት ክፍል ቤት ውስጥ ተጣበን ነው የምንኖረው። ከዚህ የተነሣ ምቾት አልባነቱን ልንቋቋመው አልቻልንም። ስንጯጯህ ነው የምንዉለው። ያች ክፍል ሲዖል ሆናብናለች።

"ችግርህ መፍትሄ አያጣም፤ ግን አድርግ የምልህን ሁሉ ለማድረግ ቃል ትገባለህ?"

"እንዴታ! እምላለሁ!"

"መልካም፤ ስንት የቤት እንስሶች አሉህ?"

"አንዲት ላም፤ አንድ ፍየልና ስድስት ዶሮዎች"

"ከዛሬ ጀምሮ እነርሱም ከእናንተ ጋር ማደር ይጀምሩ፤ ከሳምንት በኋላ ታዲያ ተመልሰህ ና፤ ሁኔታውንም ንገረኝ"

ችግረኛው ሰው በዚህ ምክር ከመጽናናት ይልቅ ይበልጥ ግራ ተጋባ። ቢሆንም አንድ ጊዜ ተስማምቷልና የገባውን ቃል ለመጠበቅ ወሰነ። እናም እንስሶቹን ማታ ማታ እዚያችው ክፍል ውስጥ እያስገባ ማሳደር ጀመረ።

እንደ ዓመት የረዘመበትን አንድ ሳምንት ከጨረሰ በኋላ ወደ ጥበበኛው ሲመለስ የበለጠ ነጭናጫ ሆኖ ነበር። መቀመጥም ሳያስፈልገው ገና እንደገባ እንዲህ አለው።

" ችግሩ ጭራሽ ተባብሷል፤ መቋቋምም ተስኖኛል። ጭቱ፤ ግማቱና ጩኸቱ መጠን የለውም። ሁላችንም ልናብድ አንድ ሐሙስ ቀርቶናል!"

"በል አሁን ወደ ቤትህ ተመለስ፤ ከዛሬ በኋላ እንስሶቹን ከቤትህ አስወጣቸው። እናም ነገ ብቅ በልና ያለውን ለውጥ አጫውተኝ"

ችግረኛው ሰው በፈጣን ሩጫ ወደ ቤቱ ሄደ። በሚቀጥለው ቀን ሲመለስ ዐይኖቹ በደስታ ያበሩ ነበር። ለጥበበኛውም ሲቃ በሚተናነቀው ድምፅ ይህን አበሠረው።

"ሕይወት እንዴት ትጣፍጣለች? እንስሶቹ ወጥተዋል። ቤቱ ፀድቷል፤ ጸጥታ ሰፍኖአል፤ ለሁላችን በቂ ቦታ አለ!"።

## ምን ያስተምረናል?

ከዚህ ችግረኛ ሰው ሕይወት የምንማረው የመጀመሪያ ነገር አመለካከቱ መቀየሩን ነው። በመሠረቱ ለጥበበኛው ያጫወተው ችግር አልተወገደም። አሁንም እርሱ ባለቤቱ ልጆቹና እማቶቹ በዚያችው አንዲት ከፍል ቤት ውስጥ ተጣበው ነው የሚኖሩት። ግን ምክሩን በሥራ ላይ በማዋል ችግሩን ከሌላ አቅጣጫ መመልከት በመቻሉ አመለካከቱን ቀየረ። የባሰም አለና አገርን አለመልቀቅ ይበጃል ወደሚል የሚያዛልቅ ድምዳሜ ደረሰ። ምናልባትም እሱ ከሚኖርበት ሁኔታ በባሰ እኳኋን የሚኖሩ መኖራቸውን ሳያያቸው ተረዳ።

## ንጉሡን አሳዩኝ!



ገበሬው ዙሪያ ገባውን ሳይመለከት ሥራውን በብዙ ትጋት ሲያከናውን ሳለ ከከተማ ለአደን ብቅ ካለው ትልቅ ሰው ጋር ይገጣጠማል። ያም ትልቅ ሰው በአርሶ አደሩ ሥራ ወዳድነት በማሣው ለምነትና በአካባቢው ምርት ይማረከና ገበሬውን ጠጋ ብሎ ያነጋግረዋል። ጥቂት ካወጉም በኋላ "ለመሆኑ ኑሮህ እንዴት ነው?" ሲል ትልቁ ሰው ይጠይቀዋል።

"ይመስገነው፤ ችግር የለብኝም" ይላል ገበሬው በምላሹ።

"ወደ ከተማ ወጣ ብለህ ታውቃለህ?"

"ኧረ በጭራሽ"

"አትፈልግም ማለት ነው?"

"በማን ዕድሌ ግን እዚህ ሥራው ብዙ ነው"

"ብትሄድ ግን ለማየት የምትጓጓው ምንድነው?"

"ንጉሡን ባያቸው ደስታውን አልችለውም"

"እንግዲያው እኔ አሳይሃለሁ፤ እንሂድ" ይልና ትልቁ ሰው ገበሬውን በበቅሎው አፈናጥጦት ጉዞ ይጀምራሉ።

ወደ ከተማው መግቢያ እንደደረሱም "ሰው ሁሉ ንጉሡን ሲያይ ወድቆ እጅ ይ ነሣል፤ በበቅሎና ፈረስ የሚጓዙትም እሱን ሲያዩ ይ ወርዱና ሰላምታ ይሰጡታል። በዚህም ንጉሡን መለየት ትችላለህ" ይለዋል።

ጥቂት እንደተጓዙ ሰው ሁሉ ባለበት አያጎነበሰ የሚሄዱም ከበቅሎና ፈረሱ እየወረደ እጅ ሲነሣቸው ይጀምራል። እናም ያ ትልቅ ሰው "አሁንስ ንጉሡን አየኸው"

በማለት ገበሬውን ይጠይቃል። ገበሬውም አፈፍ ብሎ "አርስዎ ጌታው እንዳሉኝ ከሆነ ሁሉ ንጉሡን ሲያይ ወድቆ እጅ ይነሣል፤ በበቅሎና ፈረስ የሚጓዘውም ይወርዳል። አሁን የማየው ሕዝቡ ለእኛ ሲሰግድ አንደ መሆኑ እንግዲህ ንጉሥ ወይ እኔ ወይ አርስዎ ነን ማለት ነው" ሲል ይመልሳል። ንጉሡም በዚህ ገበሬ የዋህነት ተገርሞና ስለ ታታሪነቱ ሸልሞ ወደ መኖሪያው መልሶታል ይባላል።

## ምን ያስተምረናል?

ገበሬው የተፈናጠጠው በንጉሡ በቅሎ ነበር። ግን አላወቀውም። የተሰጠው ምልክትና ገለጻም ለባሰ ስሕተት ዳርጎታል። ንጉሡ ግን በዚህ ተገረመ እንጂ አልተናደደም። ለምን ቢባል ገበሬው መሳሳቱ ካለማወቅ የመነጨ አንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ ይቅርታ ያደረገለት በደስታ ነው።

የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ የሆነው ኢየሱስም ለእኛ ተመሳሳይ ቸርነት አድርጎልናል። ስለሆነም ባለማወቅ ያደረግነው ሁሉ በይቅርታ ተደምስሷል። "እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት እሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል" የሐዋ. 17:30።

## ይቅር ተብያለሁ!



በጥፋቱ ለዓመታት በእሥር ቤት የማቀቀ አንድ ወጣት ለአባቱ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፈ።

" መቼም የማይደርስ የለም። እነሆ የምፈታበት ቀን ደርሶአል። ይህ ሁሉ መከራ የደረሰብኝ ግን ያንተን ምክር ባለመስማቴ ነው። አናም አባቴ ሆይ እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ፤ ለዚህ ደብዳቤዬ መልስ አልፈልግም። ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰውና በምፈታበት ቀን በባቡር በቤታችን በር ላይ አልፋለሁ። በደሌን ይቅር ካልከኝ በራችን ላይ ባለው ትልቅ ዛፍ ላይ ነጭ ጨርቅ አንጠልጥልበት። እኔም ያንን ካየሁ ወርጄ አመጣለሁ። ካላየሁ ግን ተመልሼ ላልመጣ ጉዞዬን አቀጥላለሁ።"

በተቀጠረው ቀን ወጣቱ ተፈታና ከወኅኒ ቤቱ ውጭ ያለውን ንጹሕ አየር ለመተንፈስ ዕድል አገኘ። ወዲያውኑም ጊዜ ሳያጠፋ ባቡር ላይ ተሳፈረ። ከረጅም ጉዞ በኋላ ባቡሩ ወደ ቤቱ ሲቃረብ ግን የዚህ ወጣት ልብ ከበሮ መደለቅ ጀመረ። አርሱ ለመመልከት ባለመድፈሩም መስኮቱ አጠገብ የተቀመጠውን ተሳፋሪ " እባክህ አዚያ ማዶ ካለው ቤት ፊት ለፊት ከትልቁ ዛፍ ላይ ነጭ ጨርቅ ተሰቅሎ አንደሆነ አይልኝ" ብሎ ጠየቀው። ሰውየውም ልመናውን ተቀብሎ ዐይኖቹንም ጠራርጎ አሻግሮ ሲመለከት ቆየና " ነጭ ጨርቅ የማየው ትልቁ ዛፍ ላይ አይደለም" አለ።

"ታዲያ የት ነው?" አለ ወጣቱ በመደናገጥ።

"ትልቁ ዛፍ፣ ትናንሾቹ ዛፎች፣ ስልክ እንጨቶቹና አበቦቹ ሁሉ አጥሩ ሳይቀር በነጭ ጨርቆች አሸብርቀዋል!"
" አመሰግናለሁ፤ ወራጅ አለ!"
" ግን ምንድነው ትርጉሙ?"
" አባቴ ይቅር ብሎኛል!"

## ምን ያስተምረናል?

በአንድ ወቅት በደላችን ከእግዚአብሔር ለይቶን ነበር። ግን እሱን ብቻ እንደበደልን አምነን ንስሐ ስንገባ በጌትነቱና በአዳኝነቱ ስናምነው የነፍሳችን ጌታ በ ይቅርታ ተቀበለን። የማይገባንን ይቅርታ እንዳገኘንና ምሕረቱ እንደበዛልን በዓይናችን አይተን አረጋገጥን። አልፈን ተርፈንም "አባቴ ይቅር ብሎኛል" የማለትን ድፍረት ያገኘነው ከዚያ በኋላ ነው።

የባቡሩ ላይ መንገደኛ ነገሩ እንዳልገባው ሁሉ በሕይወት መርከብ ላይ ከ እኛ ጋር ይንገላቱ የነበሩትም ይህንን ስንላቸው ግር ሊላቸው ይችላል። "ድኛለሁ" ስንላቸው የሆነ ሆኖ ይቅርታ የተቀበልን እኛ እውነትነቱን ጠንቅቀን እናውቀዋለን። ይልቁንም አዳኝ ፍለጋ ትቅበዘበዝ የነበረች ነፍሳችን በሚገባ ትረዳዋለች። ለመዳናችን ሌላ ነጋሪ ከቶ አያሻንም። ለአዳኛችን ክብር ለእኛም ጥቅም ይቅር ተብለናል። አሜን! " በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት



መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት" ኤፌ.1፡7።

## ወደ የት ነው?

ጥንቸል አገር ሰላም ነው ብላ ተኝታ እያለ አሁን መሬት ብትሰነጠቅስ ወደሚል ፍልስፍና ትገባለች።ያ ከተፈጠረ መግቢያ እንደሌላት በማሰላሰል ራሷ በፈጠረችው የስጋት ማዕበል ስትንገላታ ላለ ደግሞ ከተጠለለችበት ዛፍ ላይ አንዲት ፍሬ ወድቃ አጠገቧ ታርፋለች። ይህ ያስደነገጣት ጥንቸል ባለ በሌለ ኃይሏ መሮጥ ትጀምራለች። አሯሯጧ ያላማራቸው የዱር እንስሳት በየተራ ምን እንደሆነች ይጠይቋታል። አርሷም ፍጥነትዋን ሳትገታ "መሬት ተሰንጥቃለች፤ አምልጡ!" እያለች መሮጧን ትቀጥላለች።

አናም ቀስ በቀስ የተለያዩ እንስሳት ስለተከተሏት ጫካው ተተራመሰ። አቧራው ጨሰ። ይህንን ከሩቅ የተመለከተው አንበሳ "ምን ሆናችኋል" ሲል በታላቅ ጩኸት ይጠይቃል። እንስሶቹም በአንድ ድምፅ "መሬት ተሰንጥቋል፤ አምልጥ!" ይሉታል። አንበሳ ግን ከመሮጥ ይልቅ "የት ቦታ ነው የተሰነጠቀው" በማለት ሌላ ጥያቄ ያቀርባል። በዚህ ያልተደሰቱት እንስሶች "የትም ይሁን የት ምን ያደርግልሃል?

ይልቅ ሩጥና አምልጥ!" ብሰው ይመልሱለታል። ይህኔ አንበሳ መንገዳቸውን ዘግቶ ያቆማቸዋል። ከዚያም ማን ከማን እንደሰማ አጣርቶ ጥንቸልን በታውን ወሰዳ እንድታሳየው ያዘል። እዚያ ሲደርሱ ከወደቀችው ፍሬ በቀር ምንም ችግር አልነበረም።

## ምን ያስተምረናል?

"በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፥ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም" ሉቃ.13:24። በተለይ የዘላለምን ሕይወት የሚወስነውን ሩጫ ስንቀላቀል "ወደየት ነው" ለማለት መድፈር የግድ ይሆናል። ብዙኀኑ ስላሉበት ብቻ አንድ መንገድ ትክክል ነው ማለት ሞኝነት ነው። በዓለም መንገድ ለመሄድ ጥበት የለም። ስደትም አይታሰብም። በጠባቡ ጎዳና ሲኬድ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው።

ዘማሪዋ ሊሊ "የማይሆነው ሳይሆን የሚሆነው ላይቀር፤ ምንድነው መጨነቅ ምንድነው መሸበር?" ስትል ያዜመችው ያለምክንያት አይመስለንም። ዛሬም መንገድ ዘግተው ሩጫው ወዴትና ለምን እንደሆነ የሚያጣሩ አናብስት ያስፈልጉናል!

## ልናይ ኋላ



ስለ ሁለት ፍቅረኛሞች የሚነገር አንድ ቀልድ አለ። ወደ ጫካ ሄደውና በለመለመው መስክ ላይ ተቀምጠው ሲጫወቱ በርካታ ወጎችን ተጋርተው ነበር። በተለይም ተቃቅፈው ንጹሑን ነፋሻ አየር ሲምጉ ስሜታዊነት ተጠናውቶአቸው ነበር። ምድሩን ለቅቀው ወደ ራሳቸው ዓለም ገብተው ነበርና ስለሚናገሩት ነገር ብዙም አልተጨነቁም። እናም ቃል ኪዳናቸውን "ከሞትን አያሳየኝ፤ ከአንተ እኔን ያስቀድመኝ" በሚሉ ዓይነት ንግግሮች ሲለዋወጡ ሳለ አንድ አዳኝ(ኝ ይጠብቃል) ከተፍ ይላል።

"እጅ ወደ ላይ!"

"ምን አጠፋን?"

"እሱ ሌላ ጥያቄ ነው፡ አሁን አንድ ሰው ማሰናበት አምሮኛል፤ ከሁለታችሁ ማንን ልግድል?"

"እኔ የምጦራት እናት አለችኝ" አለች ሴትዋ።

"ማየት የተሳነው አባት አለኝ፤ ሌላ ልጅ የለውም፤ የርሷ ቤተሰብ ግን አንድ ቁና ነው" አለ ወንድየው።

"እኔ ክርክር አልፈልግም፤ ማንን ልግደል? ያለበለዚያ ራሴ መርጣለሁ"።

" ከሞትን አያሳየኝ ብሎአል፤ ስለዚህ እሱን ግደለው!"

"ከአንተ እኔን ያስቀድመኝ ስትል ነበር፤ እንደ ቃልዋ አስቀድማት!"

"ጊዜዬን አታጥፉብኝ፤ አንድ ሰው ምረጡ ነው የምለው!"

"በቃ አሏን ግደላት!"

"የለም፤ እሱን ግደለው!"

"ይኸው ነው በቃ" አለ አዳኙ እየሳቀ " ከዛፉ ኋላ ተቀምጬ የምታወሩትን ሳዳምጥ ነበር። ያ ሁሉ መሐላና ግዝት ለዚሁ ነው? መልቲ ሁላ፤ በሉ ከዚህ ጥፉ!"።

## ምን ያስተምረናል?

"ወርቅ በእሳት ይፈተናል" የሚል አባባል አለ። እውነተኛ ፍቅር በመከራ ቀን አብሮ የሚቆም እንጂ በሰላሙ ዘመን ብቻ የሚያሟሙቅ አይደለም። ደረታቸው በሜዳሊያ የተንቆጠቆጠ ተዋጊዎች በጭንቅ ቀን ደምቀው ያበሩ ናቸውና ስለአገር ፍቅር ሲያወሩ ያምርባቸዋል። አጠገባቸው የወደቀው ቁስለኛ አንዲት ጽዋ ውኃ ሲለምን መሬት በአረር ለትነድ በሬሳ ላይ ተረማምደው የጠላትን ፈንጂ ረግጠው ምሽጉንም ደርምሰው ድልን ለወገናቸው ያበሰሩ አንበሶች እንጂ የመሸታ ቤት ደንበኞች አይደሉም። የሰደት ማዕበል ገለባውን ይለያል። ጀግኖች ሲሸለሙ በቅቧቶች ያፍራሉ። በሰላሙ ጊዜ ብዙ የ ደሰኮሩ ጭንቅ ሲመጣ መግቢያው ይጠፋቸዋል። በነጻነት ዘመን ቦታ ጠበበን የሚሉ የአፍ ከርሰቲያኖች ሰደት ሲመጣ ፈጥነው አድራሻቸውን ይቀይራሉ። ብን ብለውም ይሰወራሉ።

## የሚጠብቀን አይተኛም!



በሺሕ ከሚቆጠሩት አንዱ የፌስ ቡክ ወዳጄ የላከልኝ ታሪክ ነው። አንዲት ልጃገረድ ለጨዋታ ወደ ጓደኞቿ ቤት ሄዳ ነበር። ግን ሳይታወቃትና ሳታስበው ስለመሸ በጨለማ ብቻዋን ወደ መኖሪያዋ መመለስ ነበረባት። ቤትዋ ብዙም ስለማይርቅ ደግሞም መንደሯ ትንሽ ስለሆነች በጉዞዋ ምንም ስጋት አልነበራትም። ሆኖም በሰላም ቤቷ እንዲያገባትና ከክፉም እንዲጠብቃት ወደ አምላኳ ጸለየች። ከዚያም ቀጥታውን መንገድ ትታ በአቋራጭ መራመድ ጀመረች። ግን ብዙም ሳትርቅ ነበር ጨለማውን ተገን አድርጎና ሰው የሚጠብቅ መስሎ የቆመ አንድ ሰው የተመለከተችው። ይህ ለለቀፈፋት አንደገና በጥበቃው ይከልላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች። ወዲያውኑም ውስጧ በሚያጽናና ሰላምና ጸጥታ ተሞላ። አብሮአት የሚሄድ ሰው ያለ መስሎም ተሰማት። አቋራጩን መንገድ ጨርሳ በሰውየውም አጠገብ አልፋ በሰላም ወደ ቤትዋ ደረሰች።

በሚቀጥለው ቀ ን ግን አንዲት ልጃገረድ በዚያ አቋራጭ መንገድ ላይና በዚያው ምሽት የመደፈሯን ዜና አንድ ጋዜጣ ለገፀ ንባብ አበቃ። ወንጀሉ የተፈጸመው ደግሞ ይህች ልጃገረድ በመንገዱ ካለፈች በኋላ በሃያ ደቂቃ ልዩነት ነበር። በዚህ ዜና እጅግ አዝናና በርሷ ላይም ሊደርስ ይችል እንደነበር አስባ እጅግ አለቀለች። ያዳናትን እግዚአብሔርን

እመስግና ሲታበቃ የወንጀሉ ሰለባ የሆነችውን ሌላ ልጃገረድ የምትረዳበት መንገድ ካለ ለማጠያየቅ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደች። ታሪኳንም ለፖሊሶቹ ዘርዝራ ነገረቻቸው። ይህኔ ከፖሊሶቹ መካከል አንዱ ወንጀለኛውን እንዳየችው ካረጋገጠ በኋላ ከተጠርጣሪዎች መካከል እስገድዶ ደፋሪውን ለመለየት እንድትረዳቸው ጠየቃት። እርስዋም ያለምንም ማቅማማት ተስማማች። ከቀረቡላት ምስሎች መካከል ሰውየውን ለመለየት ብዙም ጊዜ አልወሰደባትም። ግለሰቡም ይህንን ሲሰማ ወዲያውኑ ወንጀሉን ተናዘዘ። የፖሊስ መኮንኑ ይህችን ብርቱ ልጃገረድ ካመሰገናት በኋላ ከእነርሱ የምትፈልገው ነገር ካለ በማለት ጠየቃት። እርሷም ምንም እንደማትፈልግ ገልጻ ግን ለግለሰቡ አንድ ጥያቄ እንዲያቀርቡላት ተማጸነች። ለምን እርስዋን አልፎ ሌላይቱን እንዳጠቃ ለማወቅ በጣም ጓጉታ ነበር። እስገድዶ ደፋሪውም ከፖሊሱ የቀረበለትን ጥያቄ እንደሚከተለው መለሰ። " እርስዋን ያልተተናኮልኳት ብቻዋን ስላልነበረች ነው። በሁለት ረጃጅም ሰዎች ግራና ቀኝ ታጅባ ነበር የምትጓዘው!"።

## ምን ያስተምረናል?

የሚተኛና የሚያንቀላፋ እምላክ የለንም (መዝ. 121:4)። ያስማራናል፤ ይጠብቀናል፤ እስወጥቶ ያስገባናል። የሚያስፈሩ ነገሮች ሞልተዋል። እኛም ሥጋ ለባሾች ነንና



እንፈራለን። ከሌሎች የሚለየን ግን ፍርሃታችንን እንኳ ሳይቀር የምናዋየው የሚሰማ እምላክ ያለን መሆኑ ነው። በተለይም "የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና፥ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፥ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው" የሚለው ቃል እንድንጠራው ያበረታናል (1 ጴጥ. 3:12)።

## ቀበሮ መጣ!

እንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የተማርነው የእረኛው ታሪክ የማስታውሰውን ያህል እንደሚከተለው ነው። እማራጭ እጥቶ ሥራውን ቢቀበልም እንኳ ያ እረኛ ብቸኝነትን የማይወድ የመንደር ወግና ቧልት የለመደ ዝምታም የሚከብደው ቢጤ ነበር። እናም መንደርተኞቹ በጎቹን የሚያጠቃ ቀበሮ ወይም ሌላ አ ውሬ ከመጣ እንዲጮኽ መከሩት። እነርሱም ድምፁን ሲሰሙ ፈጥነው በመድረስ እንደሚረዱት ቃል ገቡለት። እናም ይሄ ሰው ለጥቂት ጊዜ እንደምንም ታግሦ ሥራውን ሲያከናውን ቆየ። ሆኖም ጥቂት ሰዓቶችን እንደገፋ ገና ከወዲሁ የቀኑ ርዝመት አስፈራው። የሚያናግረው ሰው እለመኖሩ ደግሞ ይበልጡን አስከፋው። ስለዚህ ከሰዎች የሚያገናኘውን ብቸኛ እማራጭ አንድ ጊዜ ለመሞከር ወሰነ። እናም እሪታውን በማለማት የድረሱልኝ ጥ ሪ አደረገ። መንደርተኞቹም እረኛው ጮኾ

እንኳ ሳይጨርስ ተሯሩጠው አካ ባቢውን እንደ ንብ ከበቡት። ወዲያውኑም በተሰያዩ አቅጣጫዎች ተበትነው አሰሳ ማድረግ ጀመሩ። ግን የቀበሮ ዘር ፈጽሞ አላዩም። ስለዚህ ለምን እንደጮኸ እየተገረሙ ጠየቁት። እርሱም ከልቡ እየሳቀ ድረሱልኝ ያለ ው ብቸኝነት ስለተሰማው እንደሆነ ነገራቸው። መንደርተኞቹ ግን አልሳቁም። ሁሉም የየራሳቸው ሥራ እንዳላቸው በመግለጽ ስለስንፍናው ገሥፁት። እስከትሰውም ከዚህ በኋላ እንዲህ ዓይነቱን የቀልድ ጥሪ እንዳያሰማ አስጠንቅቀውት ወደየመጡበት ተመለሱ። እርሱ ግን አላስችል ብሎት ብዙም ሳይቆይ አካባቢውን በጬኸት አተራመሰው። መንደርተኞቹም ከላይና ከታች ተሯሩጠው ደረሱለት። ጥሪው የሐሰት መሆኑን ስመረዳት ግን ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም።

በተደጋጋሚ ይህንኑ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ ግን በመጨረሻ የተፈራው ነገር ደረሰ። ወሳኙ ሰዓት መጣ። ቀበሮ በጎቹን ስመንጠቅ ብቅ አለ። እረኛውም ከሌላው ጊዜ በተለየ አኳኋን ባለ በሌለ ኃይሉ ጮኸ። መንደርተኞቹ ግን አልመጡም። እንደ ልማዱ ሲቀልድ ይሆናል ብለው በማሰብ ባሉበት ቆዩ። ቀበሮውም የሚፈልገውን ይዞ ሄደ።

## ምን ያስተምረናል?

መንደርተኞቹን ምን እንዳዘናጋቸው ለማወቅ ብዙ ምርምር አይሻም። እረኛው በተደጋጋሚ እየጮኸ



ስላደከማቸው እነርሱም በእረኛው ላይ አመኔታ ስላጡ ነው። ውሸታምን ሰው ማንም ሊታመንበት አ ይችልም። እንደጥሩ ዜጋ አገርን ሰማገልገልም ይሁን በሕዝብ ዘንድ አመኔታ ሰማግኘት እውነትን መናገር ቁልፍ ጉዳይ ነው። ይልቁንም የወንጌልን እውነት የሚመሰክር ሰው ኑሮውን በውሸት ሊመራ አይችልም። " ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ" ኤፌ.4:25።

## የሰው ሰውነቱ

ግለሰቡ በፀጥታ የሚሠራው ነገር ኖሮት ይሁን ወይም ለብቻው መሆን ፈልጎ ባይታወቅም አንድ ሆቴል ውስጥ ክፍል ይከራይና ያድራል። በሆቴሉ ሕግ መሠረት ከፍሉን በዕለቱ የሚለቅቅ ሰው ከምሳ በፊት ቁልፉን ማስረከብ አለበት። ያ ሰው ግን ለቁርስ እንኳ ከክፍሉ አልወጣም።

በተለያየ ሰዓት የጽዳት ሠራተኞች የጥራት ተቆጣጣሪዎችና ኃላፊዎች በሩን ቢያንኳኩም አልከፈተም። ግን ሁኔታው ስለረበሸው እንዲህ የምትል ማስታወሻ ጽፎ በበሩ ሥር አሾለከ። "ለጥቂት ጊዜ ልትታገሡኝ ትችላላችሁ?"። ሠራተኞቹም አጋጣሚውን ተጠቅመው መልሰው ማስታወሻ ሰደዱለት። "የመልቀቂያ ሰዓትህ

አልፏል፤ አሁንም በፍጥነት ልቀቅ!"። ከዚያ በኋላ የእንግዳውና የሆቴሉ ሠራተኞች ንግግር በወረቀት ሆነ። እንዳለቀቁት ያየው እንግዳ በመጨረሻ ለየት ያለ መልእክት ላከ። "ይህንን ሆቴል ልገዛው እፈልጋለሁና ዋጋውን ንገሩኝ!"። ሠራተኞቹ የእንግዳው ድፍረት ገርሟቸው ጉዳዩን ከሥራ አስኪያጁ ጋር ከተወያዩ በኋላ ዋጋውን ጽፈው አሾለኩለት። እንግዳው ለአፍታም ሳይቆይ የተጠየቀውን ያህል ገንዘብ ቼክ ጽፎ በበሩ ሥር ሰደደ። ሠራተኞቹ ለአለቃቸው ሲያስረክቡት እርሱ ደግሞ ከመንገድ ማዶ ወዳለው ባንክ ይሄድና የቼኩን ሕጋዊነት ይጠይቃል።

የባንኩ ሠራተኞችም በብዙ መገረም "አዎን ቼኩ ሕጋዊ ነው፡ ይህንን ለም አለማወቃችሁ ገርሞናል። ይሄኮ ታዋቂው ሚሊዮነር አከሌ ነው!"። ከዚያ በኋላ ያንን ባለጠጋ እንኳኩቶ የረበሸው የለም።

## ምን ያስተምረናል?

እንደ ማንኛውም አድሮ ሂያጅ እንግዳ የቆጠሩት ያ ሚሊዮነር በዚያኑ ቀን አለቃቸው ሆኖአል። ከሩቁ በማየት የሰውን ማንነት ለማወቅ ይቸግራል። ከመንገድ ዳር የወደቀው ጎዳና ተዳዳሪ ውስጡ በዕውቀት የታጨቀ ሊሆን ይችላል። ይልቁንም ምለኪን የሚመለለው የእግዚአብሔር ልጅ የዘላለምን ሕይወት ያህል በቢሊዮኖች የማይገዛ ሃብት ባለቤት ነው። ያም ሳይበቃ ሌሎችን እንደርሱው ወራሽ



እንዲሆኑ ወደ አምላኩ የማለጠጋት ታላቅ ዕድል ተሰጥቶታል።

"ያልታወቁ ስንባል የታወቅን ነን፤ የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፤ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ እንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው" 2 ቆሮ. 6:9-10።

## ሁሉን ለማስደሰት

ከሳሽና ተከሳሽ ፍትሕን ፍለጋ በዳኛ ፊት ቆመዋል። ዳኛውም መዝገቡን ካዩና ሁለቱም ወገኖች መቅረባቸውን ካጣሩ በኋላ ከሳሽ ክሱን እንዲያስረዳ ጋበዙት። እርሱም በብዙ ሲቃ ተከሳሹ ያደረለበትን በደል በዝርዝር አስረድቶ ጨረሰ።

ይህንኑ በጥሞና የተከታተሉት ዳኛ " ትክክል ነህ" አሉና ወደ ተከሳሹ ዞረው ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ጠየቁት። እርሱም የቀረበበት ክስ እውነትነት እንደሌለው በዝርዝር ገልጾ ጥፋተኛ አለመሆኑን በሙሉ ልብ አስረዳቸው። ዳኛውም ከመጀመሪያው ጀምሮ በመስማማት ራሳቸውን ላይና ታች ሲያወዛውዙ ቆይተው እርሱንም "ትክክል ነህ" አሉት። ይህን ጊዜ ከታዛቢዎች አንዱ የመናገር ዕድል እንዲሰጠው አስፈቀደ። ዳኛውም ለለታዛቢው

አቀራረብ ያላቸውን አድናቆት በፈገግታ ገልጸው እንዲናገር ፈቀዱለት። በዚሁ መሠረት ታዛቢው ጉሮሮውን ካጠራ በኋላ ለዳኛው ተከታዩን ጥያቄ አቀረበ። "ክቡር ሆይ፦ መጀመሪያ ከሳሹ የደረሰበትን በደልና የከሱን ጭብጥ ሰምተው ሲያበቁ ትክክል ነህ ብለውት ነበር። የተከሳሹን የመከላከያ ምስክርነት ከሰሙም በኋላ ያንኑ ደግመዋል። ታዲያ ሁለቱም ትክክል ከሆኑ ጥፋተኛው ማን ሊሆን ነው?"። ዳኛውም በበኩላቸው ለጥቂት ጊዜ ተግ ብለው ካሰቡ በኋላ አሁንም ፈገግ ብለው እንዲህ መለሱለት። "አንተም ትክክል ነህ"።

## ምን ያስተምረናል?

የዳኛው አካሄድ አስገራሚም አከራካሪም ነው። ከሳሹንም፣ ተከላሹንም ጠያቂውንም ትክክል መሆናቸውን ነገረዋቸዋል። ምን ብለው ውሳኔ እንደሚሰጡ ለመገመት ያዳግታል። ግን ሁሉን ለማስደሰት እንደሞከሩ ቁልጭ ያለ እውነት ነው። የእምነት ነገር ሲነሣም የዚህ ዓይነት አቋም ያላቸው ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። ሁሉንም ትክክል ስለሚሉት ማንም ደፍሮ በእነርሱ ላይ አይነሣም። እንዲህ ዓይነቶቹ መከባበርና መቻቻል በተሰኙ ቃላት ተጀቡነው የሚኖሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከውጭ የሚደርስባቸው ሰደት እጅግ ጥቂት አልያም ምንም ነው። እውነቱን እውነት ስሕተቱን ስሕተት የሚሉ አማኞች ግን ተወዳጆች



አይደሉም። 2 ጢሞ. 3:12 እንደሚለው "በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ"።

## ንጉሥ አይሳሳቱም

በፈረሰኛ ወታደሮች ምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘትና ሽልማትም ለመስጠት የአገሪቱ ንጉሥ በሰዓቱና በሥፍራው ተገኝተዋል። በደንቡም መሠረት የተሻለ ቀለብ በሚያገኘውና በከብር ዕቃዎች ባጌጠው ፈረሳቸው ላይ ተቀምጠዋል። ግን ምክንያቱ ሳይታወቅ ፈረሳቸው እየተቁነጠነጠ ሰላም ነሣቸው። እንዲያውም ሊጥላቸው ሁሉ ሞከረ። በዙሪያቸው ያሉ ባለሚሎችና መኳንንቱ ሁሉ ባልተለመደው የፈረሱ ጠባይ ግራ ተጋብተው የሚያደርጉት ጠፋቸው። ይህኔ ከተመራቂዎቹ ወታደሮች አንዱ ቆፍጠን ብሎ ከሰልፉ ወጣና የንጉሡን ፈረስ ልጓም ያዘ። ከዚያም እያሻሸ ለጥቂት ጊዜ በማባባል ፀጥ አሰኘው። በዚህ እጅግ የተደሰቱት ንጉሥም "እመሰግናለሁ የመቶ አለቃ" አሉት። እርሱም እንደቅድሙ ሁሉ ቀልጠፍ ብሎ ተመራቂ ወታደሮች ከሆኑት ባልደረቦቹ ሳይሆን ከ መኮንኖች ሰልፍ ተቀላቀለ።

ይህኔ ተራ ወታደር አብሯቸው መሰለፉን ያልወደዱት መኮንኖች በጥያቄ አጣደፉት።

"ወደ ቦታህ ተመለስ እንጂ?"

"ቦታዬ እዚህ ነው!"

"ይህ እኮ የመኮንኖች ሰልፍ ነው"

"ዐውቄአለሁ፤ እኔም መኮንን ነኝ!"

"ተራ ወታደር ነህ እኮ"

"አይደለሁም፤ የመቶ አለቃ ነኝ!"

"ከመቼ ጀምሮ?"

"ከዛሬ!"

"እንዴት?"

"እመሰግናለሁ የመቶ አለቃ ብለውኛል ንጉሡ"

"ተሳስተው እንዳይሆን"

"ንጉሥ አይሳሳቱም!"

## ምን ያስተምረናል?

ንጉሥ የአገሪቱ መሪ ናቸውና ያሉት ይፈጸማል። ተመራቂ ወታደር የጨበጠው ይህ እውነት ትልቅ ድፍረት ሰጥቶታል። በመኮንኖቹ ማዋከብ ያልተበገረውም ለዚሁ ነው። እኛም ተመሳሳይ ድፍረት ያሻናል ባይ ነኝ። ንጉሡ ስለ እኛ የተናገረው ይፈጸማል። ለምን ቢሉ እርሱ ፍጹም ነውና አይሳሳትም።

## አልተውህም ከቶም አልለቅህም



በአንድ ወቅት ወደ እንግሊዝ አገር ለስብሰባ ጉዳይ ሄጄ ሰንብቼ ነበር። በዚያም አንዲት እንደ እኔው ጸሐፊ የሆነች የአገሬውን ሰው ለንደን ላይ ተዋወቅሁና እርሰዋ በምትኖርበት ከተማ ደርቢ ወደሚገኘው ወዳጄ ሠፈር ልትወስደኝ ተስማማች። ከረጅሙ የጎዳና ላይ ጉዞአችን በኋላ ሻይ ጠጥቼ እንዳልፍ ፈቃዷ ሆነና ወደ ቤቷ ጎራ አልኩ። እናም እርሰዋ ኩሽና ጉድ ጉድ ስትል እኔ በግድግዳው ላይ የተሰቀሉትን ሥዕሎች፤ ፎቶዎችና የተለያዩ ጥቅሶች መቃኘት ጀመርኩ። ግን አንዱ ላይ ረጅም ጊዜ መውሰዴን ጋባዤ አስተውላ " ወደድከው?" ስትል ጠየቀችኝ። እኔም በአዎንታ ራሴን ነቀነቅሁ። ከሦስት ዓመታት በኋላ ዋሽንግተን ላይ ስሞሸር ያንን አስታውሳና በትራስ ልብስ ላይ አላትማ በስጦታ ላከችልኝ። ጽሑፉም እንዲህ ይነበባል።

" አንድ ሰው በአንድ ምሽት የሚከተለውን ሕልም አለመ። በባሕር ዳርቻ ካለ አሸዋ ላይ ከኢየሱስ ጋር የሚራመድ ይመስለዋል። በዚያኑ ቅፅበት ደግሞ ያለፈ ታሪኩን የሚያሳይ ፊልም መሰል ትርዒት በሰማይ ላይ ይመለከታል። እናም ለእያንዳንዱ የሕይወት ጉዞ የሁለት ሰዎችን የእግር ኮቴ ያያል። አንዱ የራሱ ሌላው ደግሞ የጌታ ኢየሱስ እንደሆነም ይረዳል። የመጨረሻው ትዕይንት ሲመጣ ኮቴዎችን ልብ ብሎ ሲመለከት አንድ ትልቅ ለውጥ ያስተውላል። ይኸውም ጥቂት ለማይባሉ ጊዜያት ኮቴዎቹ የአንድ ሰው ብቻ እንደነበሩ ነው። ይባስ ብሎም እነዚህ

ጊዜያት በሕይወቱ ትልቅ አደጋና ፈተናን የተጋፈጠባቸው መሆናቸውን ተረዳ። ሁኔታው እጅግ ስለከነከነው ታዲያ ለጌታ እንዲህ ሲል ጥያቄውን አቀረበ። " ጌታ ሆይ፡- አንድ ጊዜ አንተን ስመከተል ስወስን ሁሌም አብረኸኝ እንደምትሆን ቃል ገብተህልኝ ነበር። ታዲያ አሁን እዚህ የአንድ ሰው ኮቴ ብቻ የማየው በአስቸጋሪ የሕይወቴ ዘመናት ነው። በጣም በ ምፈልግህ በነዚያ ፈታኝ ቀናት ለምን እንደተውከኝ አልገባኝም?"።

ጌታም እንዲህ ብሎ መለሰለት። " የተወደድክ ልጄ ሆይ፡- አዎን እወድሃለሁ። ደግሞም አልተውህም። በአስቸጋሪ የሕይወትህ ዘመናት የአንድ ሰው ኮቴ ብቻ የምታየው እኔ ተሸክሜህ ስለነበር ነው። ያ የኔ ኮቴ ነው!"

## ምን ያስተምረናል?

እዎን፡- አብሮን የሌለ ቢመስልም ግን ጌታ ሁልጊዜም አብሮን አለ። ቃሉ እንደነገረን "... እርሱ ራሱ፤ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና " በዚህም እስከ መጨረሻው ሳይለየን ቃል ገብቷልና ያለውን ያደርጋል (ዕብ. 13:5)። የማይሻር ቃሉን ይፈጽማል። ደግሞ9ም የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚነግረን "ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን? (ዘኁ. 23:19)።



## ለሚመጣው ትውልድ

ሽማግሌው መሬቱን እ የማሉ የ ተለያዩ የዛፍ ችግኞችን ይተክላሉ። አፈር ያስታቅፋሉ። ውኃ ያጠጣሉ። በጥቅሉ ተግተው ይሠራሉ። ዕድሜአቸውን ከብርታታቸው ጋር እያነፃፀረ የሚደነቀው ወጣት ደግሞ ቆም ብሎ ያስተውላቸዋል። ለጥቂት ጊዜ ከተከታተላቸው በኋላ ወደ አእምሮው የመጣውን ጥያቄ እንዲህ ሲል አቀረበላቸው።

"አባቴ ለመሆኑ እነዚህ የሚተክሏቸው ዛፎች አድገው ለማፍራት ምን ያህል ጊዜ ይወስድባቸዋል?"

"እንዳንዶቹ ሃያ ሌሎቹ ሃያ አምስት ዓመት ይፈጅባቸዋል። ሠላሳም የሚፈልጉ አሉ"

"እ ረጅም ጊዜ ነው"

"አዎን እንዲያ ነው"

"ታዲያ እርስዎ ያን ያህል ቆይተው የሚበሉት ይመስልዎታል?"

"ያን ያህል እንኳ የምቆይ አይመስለኝም"

"ታዲያ ለማይበሉት ፍሬ ለምን ብለው ነው መድከምዎ?"

"እየሀ ልጄ ፍራፍሬ ስበላ ነው ያደግሁት። ስበላም ነው የኖርኩት። አሁንም እየበላሁ ነው። ታዲያ ያ ከየት የመጣ ይመስልሃል? አባቴና አያቶቼ የተከሉት ነው። እኔም በተራዬ ለልጆቼና ለልጅ ልጆቼ መትከል አይገባኝምን? "

## ምን ያስተምረናል?

መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ 13:22 ላይ "ጻድቅ ሰው ለልጅ ልጆቹ ያወርሳል፤ የኃጢአተኛ ብልጥግና ግን ለጻድቅ ትጠበቃለች" ይላል። ሽማግሌው በሥራቸው የሚያሳዩን ለእኛ የተደረገውን መልካምነት ለሌሎችም ማድረግ እንደሚገባን ነው። ወደ ወንጌል ስርጭትም ስንመጣ ተመሳሳይ ነገር ይገጥመናል። ብዙዎቻችን ከድቅድቁ ጨለማ ወደሚደነቀው ብርሃን ዘወር ያልነው በሌሎች ምስክርነት ነው። አሁን ደግሞ እኛ በተራችን የተደረገልንን መልካምነት ለሌሎች ለማካፈል ሰፊ ዕድል አግኝተናል። ቆይቶ በሰዎች ልብ ውስጥ ሠላሳ፣ ስድሳና መቶ አጥፍ ለማፍራት ብቃት ያለውን ዘር አርሱም የጌታ ቃል ለመዝራት ጊዜው አሁን ነው!

# እኛኮ አልደረስንም

ወደ አፍሪካ ለወንጌል ስርጭት የተጓዘው ሚስዮናዊ ከዘመናት አገልግሎት በኋላ ወደ አገሩ ለመመለስና ቀሪ ዘመኑን በትውልድ መንደሩ ለማሳለፍ ይወስናል። በወጣትነት ዘመኑ መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ ለዘመቻ ከተነሣበት ዘመን ጋር ሲነፃፀር ሁለት ትልቅ ልዩነቶች ነበሩ። የመጀመሪያው ዘመኑን ሁሉ ስላገለገለ አሁን አርጅቶ ነበር።



ሁለተኛው ደግሞ በወንጌል አገልግሎቱ ዘመን የወለደው ወንድ ልጁ አብሮት መመለሱ ነው።

ወራት የፈጀውን የመርከብ ጉዞ በሰላም ጨርሰው ወደ ወደቡ ሲደርሱ መውረጃው ሥፍራ በአንግዳ ተቀባዮች ተጨናንቆ ተመለከቱ። ብዙዎቹ አቅፍ አበባ ይዘው ነበር። ሆኖም ሚስዮናዊውና ልጁ ከመርከቢቱ ወርደው ከሕዝቡ ሲቀላቀሉ ማንም "እንኳን ደህና መጣችሁ" አላላቸውም። አንድም የሚያውቃቸው ወይም የሚያውቁት ሰውም በዚያ አልተገኘም።

ይህን በብዙ ቅሬታ ያስተዋለው ወጣት አባቱን "ይህን ያህል ዘመን እግዚአብሔርን አገልግለን ወደ አገራችን ስንመጣ አንድ ሰው እንኳ ያልተቀበለን ለ ምንድነው?" ሲል በትኅትና ጠየቀው።

አባቱም ብዙ ማሰብ ሳያስፈልገው እንዲህ መለሰለት "እየሀ ልጄ እኛኮ ገና አልደረስንም!!!"።

## ምን ያስተምረናል?

ሚስዮናዊው አገራችን የሚላው ከተወለደባት ምድር ይልቅ የሚሄድባትን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን ነው። ምድራዊ አገራችንን መዳረሻ ካደረግን ለማያዊውን ጉዞ አልጀመርንም ማለት ይቻላል። ለምን ቢሉ ከክብር ይልቅ ጨ ከነን ለክርስቶስ ስንኖር የሚከተለን በረከት ለደት ነው። የትኛው ሐዋርያ ነው በምድር ተከብሮ አገልግሎቱን የጨረሰ? እዚህ

ባለድንኳኖች ነን። "እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን" ፊሊጵ. 3:20።

## ስንፍና አይገባም

ሰውየው እንደተለመደው ለማለዳ ጸሎት ተራራ ላይ ወደተሠራው ቤተ አምልኮ እየተጓዘ ነው። ጥቂት ዳገቱን እንደወጣ ግን ደከመው። ስለዚህ ድንጋይ ቢጤ ፈልጎ ቁጭ አለና "እስከ መቼ ነው እንዲህ እያማጥኩ ተራራ የምወጣው? እንዲት በቅሎ ማን ገደለ? ዛሬ ተሸከሞ የሚያወጣኝን ካለሰደድከ ከዚህ አልነቃነቅም" እያለ ከአምላኩ ጋር ክርክር ጀመረ። የክርከሩ ምላሽ ግን ብዙም ሳይቆይ መጣ። አንድ ጠብደል ጎረምሳ ያለአቅሙ የተጫነ አህያ እየነዳ ደረሰ። እርሱም በተራው እንዲህ እያለ እያጉረመረመ ነበር። "አምላኬ ሆይ ይህ አህያ እየደከመ ነው፤ ዛሬ ይህን ተራራ ችሎ የሚወጣው አይመስለኝም፤ ስለዚህ ሸከሙን የሚያግዝ ጉልበታም ሰው አዘጋጅልኝ! "

ከተራራው ወገብ ላይ ሲደርስ ሰውየው ቁጭ ብሎ ሲነጫነጭ ተመለከተው።

"አንተ ደግሞ ምን ሆነህ ነው?" አለው በመገረም።



"ምን ሆንክ ትለኛለህ? በዚህ ዕድሜዬ ተራራ የምገፋው ምን በድዬ ነው? አሁንም የሚሸከመኝ ሰው ካላገኘሁ አልወጣም ብያለሁ"።

"በል የአህያዬን ሸከም አግዘው"

"አባክህ አትቀልድ!"

"ተነሣ የአህያዬን ሸከም አግዘው"

"ጭራሽ ሸከም! ራሴንም መሸከም አቅቶኛል"

"አግዘው እኮ ነው የምለው" አለ አንዴ በያዘው በትር እየጨረደው።

"እሺ እሺ እሸከማለሁ" አለና የአህያውን ጭነት ተጭኖ ተራራውን መውጣት ጀመረ።

"ረፍዶብኛል፤ ቶሎ በል" አለ ባለአህያው አሁንም አንዴ እየገሾሰጠው።

"እሺ እሺ ብቻ አትማታ" አለና በሩጫ ሸመጠጠ። ከተራራውም ጫፍ ፈጥኖ ደረሰና ጭነቱን አስረከበ። ባለአህያውም መልሶ ከጫነው በኋላ ዘወር ብሎ አጭር ምክር ሰጠው። "በእውነት የተባረከ ጉልበት አለህ፤ ግን ስንፍና አታስለምደው! "።

### ምን ያስተምረናል?

ስንፍና አይገባም። ይልቁንም ሰው ማድረግ ለሚችለው ነገር ሲሰንፍ የበለጠ አስቀያሚ ነው። ሰውየው እንኳን ባዶውን የአህያ ሸከም እንኳ ተጭኖ ተራራ

የመውጣት ብቃት ነበረው። ግን በስንፍና ተሞልቶ ከእምላኩ ጋር መጨቃጨቅ ጀመረ። ወዲያውም በቂ ጉልበት እንዳለው የሚያስታውስ መልእክተኛ ከበትር ጋር ተላከለት። መጽሐፈ ምሳሌ 19: 29 "ለሚያፌዙ ሰዎች ፍርድ ተዘጋጅታለች፥ ለሰነፎችም ጀርባ በትር" የሚለን ለዚህ ይሆን?

## ወሬኛዋ ዔሊ

ይህ በልጅነታችን ከተማርንባቸው የምሳሌ መጻሕፍት ትዝታ የተጫለፈ ነው። ዔሊዋ በመንደሩ ውስጥ የምትታወቀው በወሬኝነቷ ነበር። የባጥ የቆጡን ስትለፈልፍ ስለምትውል አፏ ጨርሶ ሥራ አይፈታም። ታዲያ አንዱን ቀን ከምትወዳጃቸው አዕዋፍ ጋር ስታወራ የዘመናት ምኞቷን እንዲህ ብላ ታጫውታቸዋለች። "እኔ ጓደኞችሁ ዕድሜዬን መሬት ለመሬት በመንቀርፈፍ ልጨርስ ነው፤ ከዚህች መንደር ወጥቼ አላውቅም። እናንተ ግን እገር ለአገር የምትበሩ ዕድለኞች ናችሁ። ለምን እንድ ቀን እንኳ ከእናንተ ጋር በአየሩ ላይ እንድንሳፈፍ አትረዱኝም? "

ወፎቹም የጥያቄዋን ከብደት ሳይከዱ ግን ወዳጅነቷን ግምት ውስጥ በማግባት በነገሩ እንደሚያስቡበት ነግረዋት ሄዱ። ቃል በገቡትም መሠረት እንድ ማለዳ ጫካ ውስጥ የሚበቅል ጠንካራ ሐረግ ይዘው መጡ። እናም እንዲህ



እሏት። "በይ እንግዲህ ይህንን መካከሉ ላይ ነከሰሽ ትይዣለሽ፤ እኛ ደግሞ እኩል ተከፍለን ግራና ቀኙን እንይዝና መብረር እንጀምራለን። ያ ማለት ደግሞ እንቺም ከእኛ ጋር ትበሪያለሽ ማለት ነው። ነገር ግን በምንም ዓይነት ሁኔታ ሐረጉን እንዳትለቅቂ! "

በዚህ ተስማምተው ጉዞው ተጀመረ። ዔሊም ለመጀመሪያ ጊዜ መሬትን ከአየር ላይ በመመልከቷ ተደሰተች። በተለይም የኖረችበትን መንደር ከፍና ዝቅ እያደረጉ እያራቁና እያቀረቡ ሲያስጎበኟት ደስታዋ ልክ አጣ። የመንደሩም ሰዎች ተጠራርተው "ብላ ብላ ዔሊም ከወፎች ጋር ትበር ጀመር" በማለት ተደነቁ። ከመካከላቸው አንዱ ግን "እንደምታውቁት ይህች ዔሊ ሲበዛ ወሬኛ ናት፣ ችግር የሚፈጠረው እንደልማዷ ልታወራ አፏን የከፈተች እንደሆነ ነው" ብሎ ሲናገር ነገሩ ከዔሊ ጆሮ ደረሰ። ዔሊም በጣም ተናዳ "አየር ላይ የማወራውና ሐረጉን የምለቀቀው እኔ ሞኝ መሰልኳችሁ" ለማለት ፈልጋ አፏን ከፈት ስታደርግ ወርዳ ከመሬት ተከሰከሰች።

### ምን ያስተምረናል?

ዔሊዋ ቃለ ምልልስ ማድረግ የነበረባት በረራውን ጨርሳ ስትመለስ እንጂ አየር ላይ ሆና አልነበረም። ወፎቹም ይህንኑ አሳስበዋት ነበር። ወደራሳችን ስንመለሰው ደግሞ ሁሉም ጊዜውን ጠብቆ ሲሆን እንደሚገባ ዘመን

የማይሽረው የእግዚአብሔር ቃል ይነገረናል። መጽሐፈ መክብብ ለሁሉ ጊዜ አለው በሚል ርዕስ እንዲህ ያብራራል። “ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው። ለመወለድ ጊዜ አለው፥ ለመሞትም ጊዜ አለው፤ ለመትከል ጊዜ አለው፥ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው፤ ለመግደል ጊዜ አለው፥ ለመፈወስም ጊዜ አለው፤ ለማፍረስ ጊዜ አለው፥ ለመሥራትም ጊዜ አለው፤ ለማልቀስ ጊዜ አለው፥ ለመሳቅም ጊዜ አለው፤ ዋይ ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመዘፈንም ጊዜ አለው፤ ድንጋይን ለመጣል ጊዜ አለው፥ ድንጋይንም ለመሰብሰብ ጊዜ አለው፤ ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፥ ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለው፤ለመፈለግ ጊዜ አለው፥ ለማጥፋትም ጊዜ አለው፤ ለመጠበቅ ጊዜ አለው፥ ለመጣልም ጊዜ አለው፤ ለመቅደድ ጊዜ አለው፥ ለመስፋትም ጊዜ አለው፤ <u>ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገርም ጊዜ አለው፤</u> ለመውደድ ጊዜ አለው፥ ለመጥላትም ጊዜ አለው፤ ለጦርነት ጊዜ አለው፥ ለሰላምም ጊዜ አለው” (3:1-8::)

ደግሞም ቃሉ ከመናገር ይልቅ መስማትን ያበረታታል። እንዲህም ይላል። “ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን” ያዕ.1:19።

## አሳዛኝ ተጓዥ



ሰውየው ረጅም የመርከብ ጉዞ ለማድረግ የብዙ ጊዜ ምኞት ነበረው። ግን ዋጋው በአርሱ አቅም የሚቀመስ አልነበረምና ገንዘቡን ለማጠራቀም ዓመታት ፈጀበት። እናም አሳቡ ሞልቶ ቲኬቱንም ቆርጦ ስንቁን የቋጠረበትን ሻንጣ ተሸክሞ መርከቢቱን ፍለጋ ወደ ወደቡ አመራ። በተያዘው ፕሮግራም መሠረትም ተመዝግቦ ተሳፈረ። እንዲህ ሆነና የአራት ሳምንቱ ጉዞ ተጀመረ።

መንገደኛው በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት በመርከቡ ምቾት፣ በውኃው ድንበር የለሽነትና በዶልፊኖች የዋና ጥበብ ሲደሰት ቆየ። የመመገቢያ ሰዓት ሲደርስ ግን መንገደኞች ሁሉ ወደ ምግብ አዳራሹ ሲያመሩ እርሱ ለዚያ የሚሆን ትርፍ ገንዘብ ስላልያዘ ወደ ትንሿ መኝታ ክፍሉ ይወርዳል። ወደ ኋላ ግን የያዘው ስንቅ እየቀነሰ መሔዱን ሲገነዘብ አቅሙን ለመቆጠብ ወደ ላይ መውጣቱን ተወ። እንዲያውም መጨረሻ አካባቢ በቀን አንዴ ብቻ እየቀመሰ አልጋው ላይም እየተኛ በትንሿ መስኮት ውቅያኖሱን በማየት ብቻ ጉዞውን ቀጠለ።

በመጨረሻ መርከቢቱ ወደ ወደቡ ተመለሰችና የጉዞው ማብቃት በድምፅ ማጉያው ተለፈፈ። መንገደኞችም በደስታ ፊታቸው ፈክቶ ጥቂት የማይባሉትም በሚታይ ሁኔታ ከብደት ጨምረው መውረድ ጀመሩ። የመርከቢቱ ካፒቴንም መውረጃው መሰላል አጠገብ ቆሞ እያንዳንዱን ተሳፋሪ በማመስገን ደግመው እንደሚመጡም ያለውን ተስፋ

በመግለጽ ሲሰናበታቸው ቆየ። በስተመጨረሻ ያ መንገደኛ በቀስስተኛ ርምጃ ወደ ካፒቴኑ ቀርቦ ተሰናበተው። ካፒቴኑም ደጋግሞ ካስተዋለው በኋላ

"ታምመህ ነበር?" ሲል ጠየቀው።

"በጭራሽ" አለ መንገደኛው።

"አንድም ቀን ምግብ ቤት ውስጥ አላየሁህም"

"አዎን የራሴን ስንቅ ስበላ ነው የቆየሁት"

"ለምን?"

"ለዚያ የሚሆን ብር አልነበረኝም"

"የጉዞ ቲኬት ቆርጠሃል አይደል?"

"በሚገባ፤ ይኸው ቀሪው!"

"ታዲያኮ ቲኬቱን ስትገዛ የከፈልከው ገንዘብ ሁሉንም ወጪህን ያጠቃለለ ነበር። በቀን ሦስቴ የመመገብ፤ ሁለት ጊዜ መቅሰስ የመብላት፣ የመዋኘት፣ በዳንስ አዳራሹና በፊልም መዝናኛው ያስገደብ የመገልገል፣ የአካል ማጎልመሻ አንቅስቃሴ የማድረግና እንዲሁም ፀጉርህን የመስተካከል መብት ነበረህ!" አለ ካፒቴኑ በጣም አዝኖ።

## ምን ያስተምረናል?

ግለሰቡ ቲኬቱን ሲቆርጥ ያላስተዋለው ጥቅማጥቅም ጎድቶታል። ይህ ደግሞ የታወቀው በጉዞው ማብቂያ መሆኑ የበለጠ አሳዛኝ አደረገው። አንዳንዶች የዘላለማዊነት ስጋት የሚገባቸው ምድራዊ ጉዞአቸውን ሲጨርሱ ሲሉ ነው።



አንዳንዶች ደግሞ ወደ ጌታ እንዲመጡ ሲጋበዙ ውጭ የለመዱት ደስታ የሚወሰድባቸው ይመስላቸዋል። ግን እውነተኛው ደስታ ያለው በእግዚአብሔር ቤት መሆኑን አያውቁም።

የበለጠ የሚያሳዝኑት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠው ከበረከት የጎደሉ ናቸው። ከዘላለም ሕይወት ጋር አብሮ የተሰጠውን ማዕቀፍ (Package) ስላላወቁ እንደ ተራ ሰው ይኖራሉ። ንስር ሲሆኑ የተገባቸው እንደ ጫጩት መሬት ይቆፍራሉ። ስለብነት ያህል እንኳ ቃሉ በሮሜ 8:32 ላይ "ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?" ይላል።

## ፈጣሪህን አሳየኝ

የተሰጠውን የማስተማር ሥልጣን በመጠምዘዝ በእግዚአብሔር እናምናለን የሚሉ ተማሪዎቹን ዕለት ተዕለት የሚያንጓጥጥ አንድ እምነት የለሽ መምህር ነበር። አንድ ቀን እንደለመደው ሁለተኛ ከፍሎችን ሲያስተምር ቆየና አምላክ የለም የሚለውን ፍልስፍናውን እያራገበ በሕልውናው በሚያምኑት ላይ ሲያላግጥ ተነሣ። ግን አልቀናውም። እንደ ሌላው ጊዜ የሚበቃውን ያህል ተሳልቆ ከመጨረሱ በፊት

በመግለጽ ሲሰናበታቸው ቆየ። በስተመጨረሻ ያ መንገደኛ በቀስስተኛ ርምጃ ወደ ካፒቴኑ ቀርቦ ተሰናበተው። ካፒቴኑም ደጋግሞ ካስተዋለው በኋላ

"ታምመህ ነበር?" ሲል ጠየቀው።

"በጭራሽ" አለ መንገደኛው።

"አንድም ቀን ምግብ ቤት ውስጥ አላየሁህም"

"አዎን የራሴን ስንቅ ስበላ ነው የቆየሁት"

"ለምን?"

"ለዚያ የሚሆን ብር አልነበረኝም"

"የጉዞ ቲኬት ቆርጠሃል አይደል?"

"በሚገባ፤ ይኸው ቀሪው!"

"ታዲያኮ ቲኬቱን ስትገዛ የከፈልከው ገንዘብ ሁሉንም ወጪህን ያጠቃለለ ነበር። በቀን ሦስቴ የመመገብ፤ ሁለት ጊዜ መቅሰስ የመብላት፣ የመዋኘት፣ በዳንስ አዳራሹና በፊልም መዝናኛው ያለገደብ የመገልገል፣ የአካል ማጎልመሻ እንቅስቃሴ የማድረግና እንዲሁም ፀጉርህን የመስተካከል መብት ነበረህ!" አለ ካፒቴኑ በጣም አዝኖ።

## ምን ያስተምረናል?

ግለሰቡ ቲኬቱን ሲቆርጥ ያላስተዋለው ጥቅማጥቅም ጎድቶታል። ይህ ደግሞ የታወቀው በጉዞው ማብቂያ መሆኑ የበለጠ አሳዛኝ አደረገው። አንዳንዶች የዘላለማዊነት ስጋት የሚገባቸው ምድራዊ ጉዞአቸውን ሲጨርሱ ሲሉ ነው።



አንዳንዶች ደግሞ ወደ ጌታ እንዲመጡ ሲጋበዙ ውጭ የለመዱት ደስታ የሚወሰድባቸው ይመስላቸዋል። ግን እውነተኛው ደስታ ያለው በእግዚአብሔር ቤት መሆኑን አያውቁም።

የበለጠ የሚያሳዝኑት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠው ከበረከት የጎደሉ ናቸው። ከዘላለም ሕይወት ጋር አብሮ የተሰጠውን ማዕቀፍ (Package) ለላላወቁ እንደ ተራ ሰው ይኖራሉ። ንስር ሲሆኑ የተገባቸው እንደ ሚጫጩት መሬት ይቆፍራሉ። ለአብነት ያህል እንኳ ቃሉ በሮሜ 8:32 ላይ "ሰገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?" ይላል።

## ፈጣሪህን አሳየኝ

የተሰጠውን የማስተማር ሥልጣን በመጠምዘዝ በእግዚአብሔር አናምናለን የሚሉ ተማሪዎቹን ዕለት ተዕለት የሚያንጓጥጥ አንድ እምነት የለሽ መምህር ነበር። አንድ ቀን እንደለመደው ሁለተኛ ከፍሎችን ሲያስተምር ቆየና አምላክ የለም የሚለውን ፍልስፍናውን እያራገበ በሕልውናው በሚያምኑት ላይ ሊያላግጥ ተነሣ። ግን አልቀናውም። እንደ ሌላው ጊዜ የሚበቃውን ያህል ተሳልቆ ከመጨረሱ በፊት

ተግዳሮት ገጠመው። እናም በእምነቱ ብርቱ ከሆነ የሰባት ዓመት ልጅ ጋር ተጋጠመ። እንዳይናገር ገድቦ የሚበቃውን ያህል ካሾፈበትና ለጓደኞቹም መሳቂያ ካደረገው በኋላ አንድ ጥያቄ አቀረበለት።

" ለመሆኑ እግዚአብሔርን አይተኸዋል?"

" አላየሁትም"

" ታዲያ ሳታየው እንዴት አለ ትለኛለህ?"

" ለማመን ማየት አያሻኝም"

" ካላየኸው መኖሩን እንዴት አወቅህ?"

" መኖሩን ለማወቅም ማየት የግድ አይሆንም"

" በል እምላክህን አሳየኝ፤ ያለበለዚያ ሁለተኛ..."

" እሺ አሳይዎታለሁ!"

" የት አለ?"

" እንውጣና ላሳይዎ"

" ፀሐይቱን ያዩአታል?"

" እዎ...ታዲያ...የት አለ...?"

" ፀሐይቱን ትክ ብለው ይመልከቷት"

" አልችልም፤ ዐይኔ ይጥፋ እንዴ?"



"ግድየለም ይዩአት፤ እዚያ ነው ያለው"

"አልችልም"

"ታዲያ ፍጥረትን እተኩረው ለማየት ከተቸገሩ እንዴት ፈጣሪን ያያሉ?"

## ምን ያስተምረናል?

የገባው ዘማሪ "የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን ይመልሳል፤ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፤ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል" ይላል (መዝ. 19:17)። በሌላም ስፍራ "የቃልህ ፍቺ ያበራል፥ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል" ብሎ ይናገራል (119:130)። ይህንን ብላቴና ከእምነት የለሹ መምህር ጋር ለመደራደር የረዳው ቃሉ ነው። ከተጻፈውም አልፎ ጥበብን ጨብጧል።

የእኛ ኃላፊነት በተቻለን መጠንና በሁሉም መስክ ምላሾችን ዝግጁ ማድረግ ነው። ይህም ስለ ተለፉችን ለሚጠይቁን እመርቂ ምላሽ ለመስጠት ከምናደርገው ዝግጅት ይጀምራል። እለን ስለምንለው የዘለዓለም ሕይወት ሰዎች ቢጠይቁን ምላሽ እንዳናጣ ያንንም በትኅትናና በአክብሮት እንድናደርገው የእግዚአብሔር ቃል በአንደኛ ጴጥሮስ ሦስተኛው ምዕራፍና አስራ አምስተኛው ቁጥር ላይ በግልጽ ይነግረናል። "ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን

ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን"።

## ሁሉ ለበጎ

ሁለት ወጣቶች ለአጭር ጊዜ ሚሲዮናዊ አገልግሎት ወደ ናይሮቢ በመጓዝ ላይ ሳሉ ያጋጠማቸው እንዲህ ነበር ።

እነዚሁ ሁለት የኮሌጅ ተማሪዎች አብረው የሚማሩና ትምህርት ቤታቸውን በአሜሪካ የእግር ኳስ ውድድር የሚወክሉ ሸጋ ተክለ ሰውነት ያላቸውም ጭምር ነበሩ። የመጀመሪያውን በረራ ጨርሰውና ለንደን ደርሰው ለማረፍ ሲሞክሩ ኃይለኛ ዝናብ ስለነበር ያን ለማሳለፍ ሲዞሩ ሌላው አውሮፕላን አመለጣቸው። ስለሆነም ለሚቀጥለው በረራ በርካታ ሰዓቶችን በአውሮፕላን ማረፊያው ለመቀመጥ ተገደዱ። ጉዞአቸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነውና ይህ ነገር ለ እነዚህ ወጣቶች አልተዋጠላቸውም። ይልቁንም ስለዚህ ጉዞ በግልም ይሁን በቡድን ለረጅም ጊዜ መጸለያቸውን ሲያስታውሱ የባሰ ተደናገራቸው።

ጊዜው እንደምንም ደርሶ ቀጣዩን አውሮፕላን ለመሳፈር ሲሞክሩ በሚፈልጉት "ኢኮኖሚ" ክፍል ውስጥ ትርፍ መቀመጫ አልነበረም። ስለሆነም በአንደኛ ማዕረግ ፊት ወንበር ላይ ቦታ ተሰጣቸው። በረራው ተጀምሮ ብዙም



ሳይቆይ አውሮፕላኑ በፍጥነት ወደ ታች መምዘግዘግ ጀመረ። አወራረዱ ጤናማ ስላልነበር ተሳፋሪዎች ሁሉ መርበድበድ ጀመሩ። ጫጫታና ጩኸት አውሮፕላኑን ሞላው። ከማንም በላይ ግራ የተጋቡት ግን እነዚያ ሁለት ወጣቶች ነበሩ። ይህን በረራ ለሰዓታት ተቀምጠው መጠበቃቸው ሳያንስ አሁን ደግሞ የመጡበትን አገልግሎት እንኳ ሳይጀምሩ ሊከስከሱ ነው። እጉረምርመው ሳይጨርሱ ከበረራው ክፍል የኳኳታ ድምፅ ሰሙ። ሳያቅማሙ ተጣቅቅሰው ወደዚያው ሮጡ። ፈርጣማ ሰውነት ያለውና እንደ ጎልያድ የገዘፈ አንድ ሰው የፓይለቱን ሥፍራ ለመንጠቅ ሲታገለው ነበር የደረሱት። ጊዜ ሳያጠፉ እነዚህ ረዣዥምና ጠንካራ ስፖርተኞች ከጠላፊው ጋር ግብግብ ገጠሙ። እነርሱ ፋታ የሰጡት ፓይለት ደግሞ አውሮፕላኑን እንደገና አቃንቶ ወደ ትክክለኛው ከፍታ መለሰው። ወጣቶቹም ከእልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ጠላፊውን በቁጥጥር ሥር አዋሉት።

### ምን ያስተምረናል?

ልናገለግለው ስንነሣ ሁሉ ነገር ያለ እንቅፋት የሚከናወን ይመስለናል። የሚታየን የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ብቻ ነው። ለነዚህም ወጣቶች መደናገር ምክንያቱ ይኸው ሳይሆን አይቀርም። ማንም በእነርሱ ሥፍራ ቢሆን ማጉረምረሙ አያስገርምም። የሆነ ሆኖ መጨረሻ ላይ የሆነውን ሲመለከቱ አሁንም እግዚአብሔር ሁሉን

በመቆጣጠር ላይ መሆኑን ሳይገነዘቡ አይቀሩም። አውሮፕላን ያመለጣቸው ኋላ ም ለበረራ መቆጣጠሪያው ሥፍራ የቀረበ ወንበር የተሰጣቸው የብዙዎችን ሕይወት ለመታደግ እንደነበር ሲገባቸው ቅሬታቸው እንደ ጉም ብን ብሎ እንደጠፋ እንጠራጠርም። "እግዚአብሔርንም ለሚወድዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን (ሮሜ.8:28)።

## ጥንቸልና ዔሊ

ከዕለታት በአንዱ ቀን ጥንቸል ዔሊን እንዲህ ስትል እንቋሸሸቻት። "አንቺ ቀርፋፋ እንዲሁ ዘላለምሽን እንደተንተተሽ አለሽ ። እኔ የምለው መቼ ነው መሮጥ የምትጀምሪው? መቼስ ነው የምትወዳደሪው?"። ግን ይህ አባባሏ አዲስ አልነበረም።

የጥንቸል አፍ አላስኖር ያላት ዔሊ አንድ ቀን እንወዳደር የሚል ጥያቄ አቀረበች። ጥንቸልም ልቧ እስኪፈርስ ስቃ ተስማማች።

እናም ውድድሩ ተጀመረ።

ጥንቸል ተፈተለከች። እቧራውን እስነሥታ በረረች። ዔሊ ደግሞ እንደተለመደው መንፏቀቋን ቀጠለች። ጥንቸል ውድድሩን ካጋመሰች በኋላ ዘወር ብላ ስታይ ዔ ሊ በአካባቢው የለችም። ስለዚህ ትንሽ ልረፍ አለችና ወደ ጥግ ወጥታ ጋደም አለች። እሯሯጧ ፈጣን ስለነበርና ስለደከማት ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰዳት።

ዔሊ በበኩሏ በተለመደው ቀስስተኛ አካሄዷ እየተንተተች ከእኩለ ቀን በኋላ ከውድድሩ ማብቂያ ደረሰች። ተሰብስበው የነበሩት እንስሳትም በታላቅ ጭብጨባ፣ ፉጨትና ድምፅ አካባቢውን አናወጡት።

ይህኔ ጥንቸል ከእንቅልፏ በርግጋ ተነሣች። እንደ ከዋክብት ተወርዉራና በ ሩጫ ገሥግሣ በሰከንዶች ልዩነት ወደ ፍጻሜው ደረሰ ች። ግን የጨረሰችው በሁለተኝነት ስለነበር መሸነፏ ተረጋገጠ። ከዚያ በኋላ ደግማ አልፎከረችም።

### ምን ያስተምረናል?

ጥንቸል ፈጣን ሯጭ ዔሊ ደግሞ ቀርፋፋ መሆናቸው ተብሎ ያስቀሰት ነገር ነው። የጥንቸል ፉከከር ከሌሎች ፈጣን ጥንቸሎች እንጂ ከዔሊ ጋር ሊሆን አይችልም። ብታሸንፍም እንኳ ዔሊን አሸነፈች ብሎ የሚያወራ ባልተገኘም ነበር። ከእኛ የሚያንሱትን እ ያየን እነርሱን ከማብጠልጠል ይልቅ የሚበልጡንን ለመፎካከር ነው መዘጋጀት ያለብን። በመንፈሳዊው ጉዞም ቢሆን የወደቁትን እንድናነሣ፣ ለደከሙት እንድንማልድና ያዘነትንም እንድናጽናና ነው ጥሪአችን። " የደከሙትን እጆች አበርቱ፥ የላሉትንም ጉልበቶች አጽኑ። ፈሪ ልብ ላላቸው። እነሆ፥

አምላካችሁ በበቀል በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና፥ መጥቶም ያድናችኋልና በርቱ፥ አትፍሩ በሉአቸው" ኢሳ.35:3-4።

## እንደ ስምህ ሁን

ናፖሊዮን የተባለውን ፈረንሣዊ ጦረኛ በጀግንነቱ ዓለም ሁሉ ያውቀዋል። ዋተርሉ ላይ በትንሽ ውጊያ ከመሸነፉ በፊት ታላላቅ ጦርነቶችን መርቶ አስደናቂ ድሎችን ተቀዳጅቷል።

ይህ ሰው ከማንኛውም የጦር መሪ የሚሰይባቸው የተሰዩ ባሕርያት ነበሩት። ከነዚህም አንዱ የተፋፋመውን ውጊያ ፊት ቀድሞ ከመምራትም ባሻገር በድንገት ወደ ኋላ ተመልሶ የጦሩን የኋላ ደጀን ዝግጅት እንዲሁም አቅርቦቱን መስለሉ ነበር።

ታዲያ አንድ ቀን እንደ ልማዱ ፈረሱን እየጋለበ ወደ ኋላ ዞሮ የጦሩን ስንቅና ትጥቅ ሲቃኝ አንድ ወጣት ወታደር ተመለከተ። በጠባቂነት የተመደበው ይህ ቃፊር ምንም አንኳ ከውጊያው በመቶዎች በሚቆጠር ርቀት የራቀ ቢሆንም ጥግ ይዞ ይንቀጠቀጥ ነበር። ምናልባትም ጠላቶቹ አጥቅተው ወደዚህ ከተጠጉ ምን እንደሚውጠው አስቦ ሊሆን ይችላል።



ለማንኛውም ናፖሊዮን ወደወጣቱ ተጠግቶ ስሙን ጠየቀው።

"ማን ትባላለህ?"

"ናፖሊዮን"

"ምን?"

"ናፖሊዮን"

"እርግጠኛ ነህ?"

"አዎን መጠሪያ ስሜ ነው"

"እንግዲያውስ ወይ ስሜን መልስ ወይ እንደኔ ሁን!"

### ምን ያስተምረናል?

ናፖሊዮን ታላቅ ጀግና ተዋጊ ሆኖ ሳለ ሞክሼው ድንጉጥ መሆኑን አልወደደውም። ስምን ቢሉ የእርሱን ስም ተሸከሟል። "ናፖሊዮን የተባሰው ጀግና" በተባለበት አንደበት "ናፖሊዮን የተባሰው ፈሪ" እንዲጠራ አልፈለገም። እናም ምርጫ ሰጠው። ወይ እርሱ ን መምሰል አልያም ስሙን መቀየር። መሆን ወይም አለመሆን ነው ጥያቄው።

እኛም ዛሬ አዳኛችንን ለመምሰል ተጠርተናል። በስማችን ክርስቲያን ተብለን በሥራችን ግን ራሳችንን ስንሆን አያምርም። ናፖሊዮን ወታደሩን እንደ እርሱ እንዲሆን ከማዘዝ ያለፈ መፍትኼ አልሰጠውም። ክርስቶስ ግን የሚያስችለንን መንፈስ ከአባቱ ተቀብሎ ልኮልናል። ይህንን በኑሮው የተገበረው ጳውሎስ በሙሉ ድፍረት "እኔ

ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ይሰናል (1 ቆሮ.11:1)።

## የጣቶች ፉክክር

አንድ ቀን አውራ ጣት ባነሣው አሳብ ጣቶች ክርክር ገጠሙ። ውዝግቡም እንደሚከተለው ነበር።

አውራ ጣት "በነገራችን ላይ ሰዎች ደስ ሲሰኙ ወይም ግብ ሲያቆጥሩ እኔን ወደ ላይ እንደሚቀስሩኝ አስተውላችኋል? በዚህ ላይ ከናንተ መካከል ወፍራሙና ጠንካራው እኔ ነኝ፤ ለዚህ ነው አውራ ወይም ዋና የሚል ስያሜ የተሰጠኝ። ስለዚህ ከዛሬ በኋላ እኔን ልታከብሩኝ ይገባል" አለ።

ሌባ ጣት "አላፊ አግዳሚውን በመጠንቆልሽ፤ ሌባ ጣት እያሉ ስም አወጡልሽ" ተብሎ የተገጠመልኝ እኔ ምን ልበል? ሰው ሁሉ እንደ ጦር የሚፈራኝ እኔን አይደለም እንዴ? የጣት መጠቋቆሚያ ሆንኩ ያለ ሰው የሚያወራው እኮ ስለ አንተ ሳይሆን ስለ እኔ ነው። እና እኔን አክብሩ ከማለትህ በፊት ሌሎች የተሻሉ መኖራቸውን ልታጤን በተገባህ ነበር። በፈረንጆቹ ዘንድ ጠቋሚ ጣት ነው የምባለው። እቅጣጫ አመላካች መሆኔ ሌላ ክብር ነው። በአማርኛ ሌባ ጣት መባሌ በስርቆት ካላስጠረጠረኝ በስተቀር ክብር የሚገባው ለእኔ ነው።



መካከለኛ ጣት "ክርክራችሁ ይደንቃል። ለመሆኑ ከሁላችሁ በቁመት የላቀ መኖሩን እንዴት ዘነጋችሁ? ከሁላችሁ ከፍ ብዬ መታየቴ እኮ በተፈጥሮዬ ለክብር መታጨቴን ይመሰክራል። ደግሞም እኮ የትጭጭት ቀለበት ሀ ብሎ የሚያርፈው እኔ ላይ ነው። በሉ ጭቅጭቁን አቁሙና እንከባበር!"

የቀለበት ጣት "ይገርማል! እኔ መቼም እናንተ የምታወሩትን ያህል መቀባጠር አልወድም። ግን በባዶ መንኳኳት ምንድነው? ለአፍታ ዘወር በሉና ተመልከቱኝ እስኪ፤ የባለቤቱ ሃብት አደራ የተሰጠው ለማን ነው? ወርቁ አልማዙና ዕንቁው ያረፈው እኮ ማንም ላይ ሳይሆን እኔ ላይ ነው። ስሜንም የቀለበት ጣት ብለውታል። አርፋችሁ እኔን አክብሩ ድሃ ሁሉ!"

ትንሿ ጣት "እኔ የሁላችሁ ታናሽ ነኝ። የማደግና ረጅም ዕድሜ የመኖር ዕድሉ ስፊ ቢሆንም እኔን አክብሩ አልልም። ግን እስኪ አንድ ጥያቄ ላቅርብላችሁ። ከእናንተ መካከል ብቻውን የወደቀ ዕቃ ማንሣት የሚችል ማነው? መልሱ ማንም ይሆናል። ስለዚህ ክብር ፍለጋ መከራከሩን አቁሙና ተባብረን እንሥራ። እንዳችን ያለሌላው ምንም ልናደርግ አንችልም"

### ምን ያስተምረናል?

ጣቶቹ የዘነጉት አንድ አካል መሆናቸውን ነው። ደግሞም ትንሿ ጣት እንዳለችው አንዳቸው ያለሌላው ምንም ሊያደርጉ አለመቻላቸውን ነው። ሰውን ሊጨብጡ፣ ዕቃ ሊያነሡም ይሁን ሊተይቡ ሲፈልጉ የትኛውም ሥራ በአንድ ጣት ሊከናወን አይችልም። በርግጥ አንዳቸው ከሌላቸው ጎላ ብለው የሚታዩበት ጠንካራ ጎን ሊኖራቸው ይችላል። አላቸውም። ያ ግን የመለያየት ምክንያት ሊሆን አይገባውም።

ብዙዎቻችን አካል በሆንንበት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ችግሮች አሉ። እኔ ከሌለሁ ይህ ቤተ አምልኮ ይዘጋል ፤ ምዕመኑም ይበተናል ብለው በእንደበታቸውም ባይሆን በሁኔታቸው ደፍረው የሚናገሩ ጥቂት አይደሉም። እነርሱ ከሌሉ የመዘምራን ቡድኑ እንደሚፈርስ የሚያስቡ ድምፃውያን አሉ። እነርሱ ዘወር ካሉ የጋዜጣና መጽሔቱ ሕትመት እንደሚቆም የሚወራረዱ ጸሐፍትም እንዲሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አያበረታታም። ለአመራር የተቀቡ ቢኖሩም ሥራው ግን እነርሱ በሌሉበትም ይቀጥላል። ደግሞም የወንጌል ሥራ የሚሠራው በሕብረት ነው። ስለ ሁሉም አስፈላጊነት ቃሉ እንዲህ ብሎ በሰፊው ያብራራልና።" አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና። እግር እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ብትል፥ ይህን በማለትዋ የአካል ክፍል መሆንዋ ይቀራልን? ጆሮም እኔ ዓይን አይደለሁምና የአካል ክፍል



አይደለሁም ቢል፥ ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መስማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መስማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ? አሁን ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብልቶችን እያንዳንዳቸው በአካል አድርጎአል። ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ አካል ወዴት በሆነ? ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች ናቸው አካል ግን አንድ ነው።ዐይን እጅን አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም፥ ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን አታስፈልጉኝም ሊላቸው አይችልም። ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው፤ ከአካልም ብልቶች ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉን በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን፥ በምናፍርባቸውም ብልቶቻችን ክብር ይጨመርላቸዋል፤ ክብር ያላቸው ብልቶቻችን ግን ይህ አያስፈልጋቸውም። ነገር ግን ብልቶች እርስ በርሳቸው በትክክል ይተሳሰቡ ዘንድ እንጂ በአካል መለያየት እንዳይሆን፥ ለጎደለው ብልት የሚበልጥ ክብር እየሰጠ እግዚአብሔር አካልን አገጣጠመው። አንድም ብልት ቢሣቀይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሣቀያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል። እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ"1 ቆሮ.12፡ 14-27።

## ፕሮፌሰሩና ጀልበኛው

ፕሮፌሰሩ ለአረፍት በሄዱበት ስፍራ በእጅ የሚቀዘፍ ጀልባ ይሣፈራሉ። ቀዛፊው በብዙ አከብሮት ደሴቶቹን እያሳያቸው ሳለ አንዳንድ ጥያቄ ያነሡበታል።

"እንግሊዘኛ ትችላለህ?"

"አልችልም ጌታዬ"

"ፈረንሳይኛስ?"

"አልችልም"

"ጀርመንስ ትሞክራለህ?"

"እርሱንም አልችልም"

"ታዲያ እንዴት ነው ከቱሪስቶች ጋር መግባባት የምትችለው? በጣም ያሳዝናል!"

እንዲህና እንዲያ እያሉ ጀልባ ቀዛፊውን በአግቦና በሽሙጥ መከራውን ሲያበሉት ቆዩ። ግን ወደተነሡበት በመመለስ ላይ ሳሉ ነገር ተቀየረ። ኃይለኛ ማዕበል ተነሣ። ጀልባዋንም እንደ ትንሽ አሻንጉሊት ይጫወትባት ጀመር። ይህኔ መጠየቅ የቀዛፊው ተራ ሆነ።

"ዋና ይችላሉ ጌታዬ?"

"በጭራሽ!"

"ታዲያ እንዴት ነው ከሞት የሚያመልጡት? በጣም ያሳዝናል!"።

<u>ምን ያስተምረናል?</u>



ቀዛፊው የቋንቋ ዕውቀት አልነበረውም፤ ግን ጀልባ መቅዘፍ እና በተሰይም ዋና ይችል ነበር። ፕሮፌሰሩ ደግሞ ቀዘፋና ዋና ቢቸግራቸውም በቋንቋዎች የተካኑ ይመስላል። ግን አያያዛቸው ትዕቢት ነበረበት። በአከብሮት ያስተናገዳቸውን ሰው ሲያንቋሽሹ ታይቷልና። ሆኖም በአፋቸው ቃል ተጠመዱና ያልዘገየ ፍርድ መጣ። ቋንቋ አለማወቅ ሞትን አያስከትልም። ግን ጀልባ ገልብጦ ሊገድል የሚችል ወጀብ ተነሣ። "አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት" (ገላ.6:7-9)።

## <u>የበለጠ ተአምር!</u>

አስተማሪው እግዚአብሔር የለም እያለ ከተሰጠው ሥራ ውጭ የተማሪዎቹን እምነት ለማጥፋት ይጣጣራል። መጽሐፍ ቅዱስን የሰዎች ፈጠራ ነው ይልቁንም አቅመ ቢሶች በቀቢፀ ተስፋ እንዲኖሩ የተጻፈ ተራ ወሬ ነው እያለ የትንንሾቹን አእምሮ ለመበረዝ ብዙ ያወራል።

በንግግሩ መካከል እንዲህ አለ። " ለዛሬ አንድ የሰየሰት ውሸት በምሳሌ ላሳያችሁ። ቀይ ባሕር ለሁለት

ተከፈለ እስራኤላውያንም በደረቅ መሬት ተሻገሩ ሲባል ለምታችኋል አይደል? ተመራማሪዎች እንደደረሱበት ከሆነ ግን እነርሱ የተሻገሩት አርባ ኢንች ጥልቀት ባለው ውኃ ላይ ነው። እናስ ብትሉኝ ጫማቸው ርሶ ካልሆነ በስተቀር ምን እንዳይሆኑ ነው ውኃው መከፈል ያስፈለገው? አመኑኝ ይህ መጽሐፍ የዚህና ሌሎችም ልቦለዶች ጥርቅም ነው።"

በዚህ ጊዜ ከትናንሾቹ ልጆች አንዱ በታላቅ ድምፅ "ሃሌሉያ!" ብሎ ጮኸ። ለምን እንደጮኸ አስተማሪው ሲጠይቀውም ምክንያቱን እንዲህ ሲል በአጭሩ ተናገረ። "እግዚአብሔር የፈርዖንን ሠራዊት፣ ፈረሶቹና ሠረገሎቹን በአርባ ኢንች ውኃ ውስጥ ማስመጡ ገርሞኝ ነው። ካነበብኩትም ይልቅ አርሰዎ ባሉት ውስጥ የባሰ ተአምር አየሁ።"

<u>ምን ያስተምረናል?</u>

አንዳንዴ የወንጌሉ ጠላቶች የሰዎችን እምነት ለማጥፋት የሚመቱት መላ ጭራሹኑ የሚያራምደው ሆኖ ይገኛል። እንደ በልቴር ማተሚያ ቤት ማለት ነው። ሰውየው መጽሐፍ ቅዱስን ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ ተፃራሪ ጽሑፎችን ሊያትም ነበር የከፈተው። እርሱ ሲሞት ግን ክርስቲያኖች ገዝተው መጽሐፍ ቅዱስ ማተሚያ አደረጉት። ይህም አስተማሪ ያጠፋ መስሎት የልጆቹም እ ምነት ከፍ አድርጓል። መዝሙረኛው "ለዘላለም ለእኔ ነውና ትእዛዝህ



ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ" እንዳለ እግዚአብሔር ለዚህ ብላቴና መምህር ነኝ ከሚለው ሰው በላይ የሚያስብ እእምሮን ሰጥቶታል (መዝ.119:98)። እንደ እርሱ ያሉ ሕፃናት በዕድሜ ከሚበልጧቸውና በልምድም ብዙ ዕውቀት ካካበቱ አረጋውያን ይልቅ አርቀው ይመለከታሉ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

## <u>ከትሉ ላለማነስ</u>

ወጣቱ በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ቢላከም በጊዜ መጨረስ ግን አልቻለም። ለምን ቢሉ ቀለም የመቀበል ችሎታው እንደ ሌሎቹ ጓደኞቹ አልነበረም። የተቻለውን ሁሉ ቢያደርግም ፈጽሞ አልሆነለትም። ስለዚህ ትምህርቱን አቋርጦ መውጣት የግድ ሆነበት።

ታዲያ ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ሳለ ይደከመውና አንድ ዛፍ ጥላ ሥር ያርፋል። ትንፋሹ መለስ ካለለት በኋላ ደግሞ እዚያው ዛፍ ላይ ለመንጠላጠል የሚሞክርን ትል ያስተውላል። ጥቂት እንደወጣ ወደ መሬት ወደቀ። ግን ተመልሶ ጥረቱን ቀጠለ እንጂ እዚያው መሬት ላይ አልቀረም። በሁለተኛው ከቅድሙ ጥቂት ከፍ እንዳለ አሁንም ወደቀ። ነገር ግን ተመልሶ ጥረቱን ቀጠለ። ዳግም በሞከረ ቁጥር መጀመሪያ ከደረሰበት ከፍታ ጥቂት ይጨምር

ነበር። በመጨረሻውና ሰባተኛ ሙከራው ተሳካለትና ከዛፉ አናት ላይ ወጣ።

ይህ ተማሪ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ሲከታተል ቆይቶ በትሉ አይበገሬነት ተደነቀ። ለራሱም እንዲህ አለ። "ይህ ትል ዛፉ ላይ ከመውጣት ይልቅ ተስፋ መቁረጥ ይቀልለው ነበር። ግን ተስፋ ባለመቁረጥ እስከ መጨረሻው በመቀጠሉ ተሳካለት። ታዲያ እኔ በመሬት ከሚሳብ ትል እንዴት አንሳለሁ? በርግጥም ተመልሼ ትምህርቴን መቀጠል አለብኝ። ደጋግሜ ተስፋ ባለመቁረጥ ከተጋሁ ይሳካልኛል! "

## ምን ያስተምረናል?

የምንኖረው በተስፋ መቁረጥ ከተከበበ ደሴት ውስጥ ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰዎች ስለ አካባቢያቸው፣ ስለ ዓለም ኢኮኖሚና ሰላም፤ ስለ አገራቸውና ስለ መጪው ዘመን ተስፋ የቆረጡበት ወቅት ነው።

ይህ ወጣት ግን ትንሽ ከምትባለው ፍጡር ተምሮ ተስፋ መቁረጥን ደህና ሰንብት ብሎታል። አንዳንድ ጊዜ ከሰው ምሳሌ ሲጠፋ ወደ ትንንሾቹ ፍጡራን እንደንመለከት ቅዱስ ቃሉም ያበረታታል። "አንተ ታካች፥ ወደ ገብረ ጕንዳን ሂድ፥ መንገድዋንም ተመልከተህ ጠቢብ ሁን። አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች፥ መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች (ምሳ.6:6-8)።



# ይቅርታ ፈላጊዎች

በአባትና በወንድ ልጁ አናጋው መካከል የነበረው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደፈረሰ ሄደ። የሚስማሙበት ነገር አነሰ። አለመግባባታቸው ከረረ። ይህን መታገሥ ያልቻለው ልጅ አንድ ቀን ተነሥቶ ከቤት ወጣ። ግን አልተመለሰም። ቀናት ሳምንታትን ሳምንታት ወራትን ወራትም ዓመታትን ቢወልዱም ወደ ቤቱ አልተመለሰም።

በዚህ ሁኔታ ስጋት የገባውና የቤተሰቡም ጉትጎታ ዕረፍት የነሣው አባት ልጁን ወደ ቤት ለመመለስ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበት አመነ። እናም ወደ አንድ የጋዜጣ አዘጋጅ ዘንድ ሄደና እንዲህ የ ሚል ማስታወቂያ እንዲያወጣለት ጠየቀ። "ልጄ አናጋው ሆይ፡- ይቅርታ አድርጌንልሃል። እስካሁን ለሆነውም ምንም ዓይነት ጥያቄ አናቀርብልህም። ወደ ቤትህ ብቻ ተመለስ። የዛሬ ሳምንት ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን በዚህ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በር ላይ እጠብቅሃለሁ።"

በሳምንቱ የጋዜጣው የዝግጅት ክፍል እኔ አናጋው ነኝ በሚሉና አባታቸውን በሚጠብቁ በርካታ ሰዎች ተሞላ!

## ምን ያስተምረናል?

ፍች ጣራ የነካው ስለ ምንድነው? የይቅርታው በር ተከርችሞ ስለተዘጋ የልጆችም መፃዒ ዕድል ስለተዘነጋ ነው። እርስ በርስ መስማማት ያቃታቸው ግን ከ ወንጌሉ ቀለብ የሚለፈርላቸው ባለሚሎች ከሰኞ እስከ ዓርብ ፍርድ ቤት የሚመላለሱት ለምንድነው? ይቅር መባባል እቅቷቸው ነው። አገር ከአገር ሕዝብ ከሕዝብ ብሔር ከብሔር ቤተሰብ ከጎረቤት እ ለቃ ከምንዝር ደጋፊ ከተቃዋሚ እርስ በርስ የሚናከሰው ስለ ምን ነው? ። ይቅርታና ምሕረት ከብዙዎች መዝገበ ቃላት ላይ ስለተፋቀ ነው። ከዚህም የተነሣ ምድራችን ከምግብ ይልቅ ይቅርታን በተራቡ ከውኃ ይልቅ ምሕረትን በተጠሙ ሰዎች ተሞልታለች። ቃሉ ምን ይለናል? "እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ" (ቆላ.3:13)።

## ዘወር በልልኝ

ንጉሡ ዜጎቹን ለበጎ ሥራ ማደፋፈርና ማበረታታት ይወድ ነበር። በ እንድ አጋጣሚ ደግሞ በሥራው እየላቀ የሄደውን የአገሩን ፈላስፋ ዝና ሰምቶ በጣም ይደሰታል። እናም እንድ ማለዳ ሊፈልገው ያለበት ድረስ ይጓዛል።

ፈላሰፋው ደጅ ተቀምጦ የፏሏን ፀሐይ እየሞቀ ነበር። ንጉሡ እጠገቡ እንደደረሰ "ለለ ሥራዎችህ



ለምቻለሁ። በርታ! አሁንም የሚያስፈልግህ ነገር ካለ ሁሉን ልሰጥህ ዝግጁ ነኝና ጠይቀኝ" ይለዋል። ፈላስፋውም ምንም ሳያመነታ "እዎን ንጉሥ ሆይ የሚያስፈልገኝ ነገር እለ፤ ይኸውም ፀሐይዋን እንዳልሞቅ ስለከለልከኝ ዘወር በልልኝ" አለው ይባላል።

### ምን ያስተምረናል?

ታሪኩን እቅልለን ካየነው ይህ ፈላሰፋ ለንጉሡ ልግሥና ንቀት ያደረበት ሊመስለን ይችላል። እርሱ ግን ከዚያም የዘለለ ነገር በዙሪያው ለተኮለኮሉ ሰዎች እያስተማረ ነበር። ማተኮር የሚያሻን በምቾት ጉዳይ ላይ ላይሆን ለዛሬ በሚያስፈልገን ነገር ላይ ነው እያለ ነበር። ለንጉሡም የነገረው ይህንኑ ነው። የፏፏ ፀሐይ በጊዜ ካልሞቋት ትጠልቃለች። የንጉሡ እቅርቦት ግን ከሰዓት በኋላም ቢሆን ይደርሳል።

መጽሐፍ ቅዱስም ከዚህም የዘለለ የሚያሳርፍ ደግሞም ተመሳሳይ መልእከት እለው። "ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ ወደ ዓለም ምንም እንኳ እላመጣንምና፥ እንዳችንም ልንወስድ እይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል (1 ጢሞ.6፡ 6-8)።

## እስራለሁ አታስሪም

ሴትየዋ ጥጥ ትፈትላለች። ባል ደግሞ ከሥራ ተመልሶ ከመደቡ ላይ አረፍ ብሏል። ከፈትሉ ጋር ከፍ ዝቅ የሚለውን ዜማዋን ለአፍታ ገታችና ወደባለቤቷ በመዞር ንግግር ጀመረች።

"አንድ አገልግል ልቃቂት ሲሞላልኝ ገበያ ወጣና እሸጠዋለሁ"

"በጄ" አለ ባልየው።

"በገንዘቡ አንዲት ሲካካ ዶሮ እገዛለሁ"

"ከዚያስ"

"ከዚያማ ዕንቁላሏን አለታቅፌ ማራባት ነው"

"ይኸው ነው?"

"ገና ምኑ ተይዞ፤ ሲያድጉልኝ እንቁላል እየለቀምኩ መቸብቸብ ነው"

"እሱ ይሻላል"

"ደግሞ ከዚያም ከዚህም አጠራቅቅምና አንዲት ጊደር እገዛለሁ"

"ጊደር?"

"አዎን ጊደር! እሷን በደንብ አሳድጌ አስጠቃትና ጥጃ ትወልድልኛለች"

"እጅብ"

"ጥጃው ብርድ ስለማይችል ከፍ እስኪልልኝ እዚህ ቤቱ መሃል ምሰሶው ላይ አሥረዋለሁ"



"እኮ እዚሁ፤ እኔ መኝታ ሥር?"

"ሌላ የት እወስደዋለሁ፤ ርጎራጌ ያሻናል"

"ብለሽ ብለሽማ ጥጃ እዚህ ቤት አታስሪም"

"እስራለሁ፤ መብቴ ነው!"

"አታስሪም!"

"አስራለሁ"

"አታስሪም!"

"እስራለሁ"

ጠቡ እየተካረረ ሄደ። ባል በምንም መልኩ የቤት እንስሳ ከእነርሱ ጋር ማደር እንደማይኖርበት አስረዳ። ሚስት ደግሞ በገዛ ቤቴ መብቴ ነው አለች። ተጣሉ። ባል ሚስቱን በሽመል ጨረገደ። እርሷም ኡ ኡ አለች።

## ምን ያስተምረናል?

ባልና ሚስቱ የተጣሉት ባልተጨበጠ ተስፋ ነው። ሚስት ብዙ ያቀደች ቢሆንም ስለ ስኬቱ ግን ማንም እርግጠኛ አልነበረም። እንዲሁ በእግዚአብሔርም ቤት ገና ይሆናል ተብሎ በሚገመት ነገር ላይ ያለው ርኩቻ አስቂኝ ነው። በአንድ ወቅት ሁለት ሰዎችን ይዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሊጀምሩ ያሰቡ ወዳጆች ወደፊት ቤተ ክርስቲያኒቱ ስታድግ ዋና መጋቢ የሚሆነው ማነው በሚል የጎሪጥ እየተያዩ ሲያወሩ ሰምቻለሁ። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ጊዜ አባካኝና አሳዛኝም ነው። ትናንት መቃብር ወርዶአል፤ ነገም

በማጎፀን ነው። በእጃችን ያለው ዛሬ ብቻ ነው። ተግተን በመሥራት ከመከናወን ይልቅ ስለ ነገ እያወራን በተረት ተረት ጊዜ እናባክን። ሁለት ምክሮች እነሆ። "ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ" 1 ጢሞ. 4:7። "ነገር ግን ሞኝነት ካለው ምርመራና ከትውልዶች ታሪክ ከክርክርም ስለ ሕግም ከሚሆን ጠብ ራቅ፤ የማይጠቅሙና ከንቱዎች ናቸውና" ቲቶ.3:9።

## የዘመናት ልፋት

ይህ ሔንሪ ማውፓሳንት ከተሰኘው ፈረንሳዊ ጸሐፊ ድርሰት የተጨመቀ ነው። ወጣት ባለትዳሮቹ የለየላቸው ድሆች ናቸው። ግን በጣም ይዋደዳሉ። በዚያ የማይረሳ ምሽት ለዳንስ ተጋብዘው ሲሄዱም ያሸማቀቃቸው ነገር ቢኖር ሌላ ሳይሆን የረባ ጨርቅ የሌላቸው መሆኑ ብቻ ነው። ያንን እንደ ምንም ካሟሉ በኋላ ቆንጆይቱ ወይዘሮ የአንገት ሐብል እንደሚያስፈልጋት ተስማሙ። ያሳቸው ብቸኛ አማራጭም መዋስ ነበር። ስለዚህ ወደሚያውቋት ባለጠጋ ሴ ት ዘንድ ሄዱ። እርስዋም ያለ የሌለ ሐብል ዘርግፋ አስመረጠቻቸው። ጥንዶቹ ዐይናቸው ያረፈበትን እንሥተው ወደ ግብዣው ቦታ አመሩ። መልካም ጊዜም አሳለፉ። ነገር ግን በመልሱ ጉዞ ከሠረገላው ሲወርዱ ሐብሉ መጥፋቱ ተረጋገጠ።



ከዚያች ቀን በኋላ ነው አኗኗራቸው ፈጽሞ የተለወጠው። የሌት ተቀን ሕልማቸው ያንን ሐብል ለመተካት ሆነ። ባሏ ሌት ተቀን በመሥራት ከሰውነት ተራ ወጣ። ወይዘሮዋም ወጭውን ለመጋራት የቤታቸው ትልቅ ቅርስ የተባለውን ፀጓሯን ተቆርጣ ሸጠች። ከዓመታት ልፋት በኋላ ገንዘቡ ሞላና ሐብሉ ተገዛ። እናም ሊመልሱ ወደአዋሰቻቸው ባለጠጋ ቤት አመሩ። በታማኝነትና በጊዜ ባለመመለሳቸው ይቅርታ ጠይቀው ሲያበቁም ያጋጠማቸውን አስረድተው ሐብሉን ለባለቤትዋ አስረከቡ። ባለ ንብረቷ ግን ከመደሰት ፈንታ አዘነች። ከመፈንደቅ ይልቅ ቆዘመች። ምክንያቱንም የገለጠችው እንዲህ በማለት ነበር። "ለምን በወቅቱ መጥፋቱን አልነገራችሁኝም? በጣም የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ነገር ነው። ምክንያቱም የተዋስሽኝ ሐብል ወርቅ ሳይሆን አርቲፊሻል ነበር። ዋጋውም ከአምስትና ስድስት ብር የማይበልጥ ነው። ብትነግሩኝ ምንኛ መልካም ነበር?"

### ምን ያስተምረናል?

ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላልና ባልና ሚስቱ የሐብሉን መጥፋት በጊዜ ቢናገሩ ኖሮ ታማኝ ከመባላቸው ሌላ ዘመናቸውን ያተርፉ ነበር (መክ.7:1)። ብዙዎቻችን እንዲሁ በማይረባ ነገር ዕድሜአችንን

እንጨርሳለን። የኋላ ኋላ ግን ለዘመናት የምንለፋበት ጉዳይ መሠረቱ አብለት ሆኖም ይገኛል።

ይልቁንም መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ያደርሳሉ ከሚለው አባባል ትይዩ እምነቶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ መስሏቸው ሲወድቁና ሲነሡ ዕድ ሜያቸውን ስለሚጨርሱ ምስኪኖች ቃሉ እንዲህ ይላል። "ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው" ምሳ.14:11።

## ተነጥላ የሄደችው በግ

ከበጎቹ መንጋ መካከል አንደኛዋ ዐይን የምትገባ ነበረች። ንጣቷና የቀንዷ ቀጥታ ከሁሉ ቀድማ እንድትታይ አድርጓታል። ስለዚህ ሁሉ ያደንቋት፤ ቅድሚያ ይሰጧትና ብሎም ይንከባከቧት ነበር። ይህ ሁሉ ተደምሮ በጊቱ እንድትታበይ አደረጋት። እናም ወጣ ስለማለት ማሰብ ጀመረች። አስባም አልቀረችም። አንድ ቀን ወገኖቿን ሰብስባ እንዲህ አለቻቸው። "ከእናንተ ጋር መኖሩ ሰለቸኝ፤ መሰማሪያም ይሁን መጠለያ ለማግኘት ከእናንተ ጋር መግተልተሉ አስመረረኝ። አንዳንዶቻችሁ ንጽሕናችሁን ስለማትጠብቁ ከእናንተ ጋር አብሮ ማደር ቅጣት ነው። ንጹሕ አየር መተንፈስም አልቻልኩም። ስለዚህ ወጣ ብዬ የራሴን ኑሮ ለመጀመር አስቤአለሁና ደህና ሁኑ! "



የመንጋው በጎች በዚህ ንግግር በጣም አዘኑ። ተለይታቸው ከመሄዷም በላይ የደነገነቷ ነገር በጣም አስጋቸው። እናም እንዲህ አሏት። "ስላልተመቸሽና እኛም የምቾት ማጣትሽ ምክንያቶች በመሆናችን ይቅርታ እንጠይቃለን። ያም ሆኖ ግን ተነጥለሽ በመሄድሽ አሳብ አንስማማም። ምክንያቱም እኛ ብዙ ጠላቶች እንዳሉን ታውቂያለሽ፤ ሌትና ቀን የሚያደቡብን የዱር አራዊት ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። ስለዚህ በአንድነት መሆናችን ይሻላል። በሕብረት ስንጮኽ ባለቤቶቻችን ይደርሱልናል። ከተነጣጠልን ግን የማንም መጫወቻ እንሆናለን። ስለዚህ አባክሽ አትሂጂ"።

በጊቱ ይህንን አሳብ ብዙ አውጥታና አውርዳ ስለነበር በወገኖቿ ልመና ፍንክች አላለችም። እናም እንዲህ ብላ ተሰናበተቻቸው። " እነዚህን ቀንዶች አዩአቸው። የተሰጡኝ ፎቶ ለመነሣት ሳይሆን ከጠላቶቼ ለመከላከል ነው። ምናልባትም ያንን ማድረግ ባልችል የሚቀርብኝ ነገር የለም። የሚጎድልብኝ ነገር ካለ የእናንተ ግፊያ ብቻ ነው። አሁን ግን ወጣ ብዬ ንጹሕ አየር ልተንፍስ አስኪ። ይልቅ ገለል ገለል ገለሰለል በሉልኝ!"

የወገኖቿን ልመና ረግጣ በጊቱ በኩራት እየተራመደች ወደ ሜዳው አቀናች። የመንጋው አባላትም በዐይናቸው ተከተሏት። ብዙም ርቃ ሳትሄድ ግን የተፈራው

ደረሰ። ራቅ ብሎ ሁኔታዎችን በንቃት ሲከታተል የነበረ ቀበሮ ዘልሎ ጉብ አለባት።

## ምን ያስተምረናል?

በጊቱ የወገኖቿን ልመና ባለመስማቷ የጎዳቸው ራሷን ነው። ምንም እንኳ ኑሮን አስቸጋሪ የሚያደርጉ እንቅፋቶችን ብትጋፈጥም መነጠል ግን መፍትኼ አልነበረም። የመንጋው ውበት በሕብረት መስማራቱ ነውና። ሌላም ያልተነሣ ጉዳይ አለ። የበጊቱ መነጠል ከሕብረት ብቻ ሳይሆን ከእረኛዋም የጥበቃ ክልል ውጭ አድርጓታል።

ቀበሮ፤ አንበሳ፣ ተኩላና ሌሎችም የበጎች ጠላት እንደሆኑ ሁሉ እኛም ጥቂት የማይባሉ ጠላቶች አሉን። "አለቆችና ሥልጣናት የዚህም የጨለማ ዓለም ገዢዎች በሰማይም ሥፍራ ያለ መንፈሳውያን ሠራዊት" ሲል መጽሐፍ ቅዱስ የሚደረድራቸው ሁሉ የእኛ ወዳጆች አይደሉም (ኤፌ.6:12)። ልክ ቀበሮው በርቀት በጊቱን ሲከታተል እንደቆየ ሁሉ የእኛም ባለጋራ የሚውጠውን ፈልጎ በአየር ላይ እንደሚያጓራ ተነግሮናል (1ጴጥ.5:8)።

ሕብረት መልካም ነው። ልክ እንደ በጊቱ እማረባችሁ ሲባሉ መለየት የሚያምራቸው ወገኖቻችን ቁጥር ብዙ ነው። አይዞህ አይዞህ የተባለው ሰባኪ ብዙም ሳይቆይ ቤተ ክርስቲያን ከፈትኩ ብሎ ላይ ታች ሲሮጥ ይስተዋላል። ከመዘመራን ቡድኑ ውስጥ የተሻለ የተባለው



ደግሞ ካሴት ላሳትም ብሎ ሲሯሯጥ ዋናውን ኃላፊነት ይዘነጋዋል። የምሳሌ መጽሐፍ " መለየት የሚወድድ ምኞቱን ይከተላል፥ መልካሙንም ጥበብ ሁሉ ይቃወማል" እንደሚል ተነጣዮች በዝተዋል (18:1)። ግድየለም አብረን እንሁን!

## ሁለቱ እናቶች

ሁለቱ እናቶች ጎረቤታሞች ናቸው። እናቶች ያልናቸው በዚያ የዕድሜ ክልል ስለሆኑ ብቻ እንጂ ሁለቱም እናቶች አልነበሩም። አንደኛዋ የሰባት ልጆች ናት። ሌላዋ ደግሞ መካን ናት። ብዙ ብትጓጓም የማኅፀንዋን ፍሬ ለማየት አልታደለችም። እንግዶችን ስትቀበል ካልሆነ በስተቀር ቤትዋ የልጆች ልቅሶ፣ የጨዋታ ድምፅና የደስታ ሳቅ ተሰምቶበት አያውቅም። ግን ምንም ማድረግ እንደማትችል ተገንዝባ ያንን ሃዘን ተቋቁማ ለመኖር ችላለች። መሸከም ያቃታት ግን የጎረቤትዋን አሽሙር ብቻ ነበር። በነጋ በጠባ አጋጣሚ ፈልጋ ትሰድባታለች። ርግማን እንዳለባት ታስታውሳታለች። በሰዎችም ፊት ታዋርዳታለች። መካኒቱ ለዚህ ምላሽ አልነበራትም። ሲብስባት ብቻ እንባዋን ታፈስስ ነበር።

የተሳዳቢዋ እናት ልጆች በሙሉ አድገው ራሳቸውን ስለቻሉ እንዴት እናታቸውን መንከባከብ ኋላም መጦር እንደሚችሉ ተመካከሩ። በዚሁም መሠረት በየሳምንቱ

በየተራ ወደ ልጆቿ ቤት እየሄደች በምቾት እንድትኖር ወሰኑ። በዚሁም መሠረት ተረኛው ልጅ ሳምንቱን ሲጨርስ እናቱን እምጥቶ በመንደር መካከል ካሰው ትልቅ የዋርካ ዛፍ ሥር አስቀምጧት ይሄዳል። ተረካቢው ደግሞ ከዚያ እንሥቶ ይወስዳትና እንክብካቤውን ይቀጥላል።

ይህ በዚህ እንዳለ ከዕለታት በአንዱ ቀን ወሳጁ ተራውን ረስቶ ሳይመጣ በመቅረቱ እናቲቱ እዚያው አድራ በሌሊቱም ቅዝቃዜ ሞታ ተገኘች። ልጆቹም ከልብ አዘኑ። ግን ከምንም በላይ ያሳሰባቸው ሰባት ልጆች ወልዳ ረዳት በማጣት ሞተች መባሉና የአገሩም ሕዝብ በእነርሱ ላይ የሚኖረው እመሰካከት ነበር። ስለዚህ በምሥጢር ሲመካከሩ አንድ እሳብ መጣላቸው። መካኒቱ ሴት በዕድሜም ይሁን በተክለ ሰውነት ከእናታቸው ጋር ተመሳሳይ ስለሆነች ማንም ሳይሰማ እሷን ወስደው እንደ እናት ሊንከባከቧት ወ ሰኑ። እናም አደረጉት። መካኒቱ ማማጥና መውሰድ ማሳደግም ሳያስፈልጋት የሰባት ልጆች እናት ሆነች።

## ምን ያስተምረናል?

መካኒቱ እለመውለዷ ሌላይቱም የሰባት ልጆች እናት መሆኗ የእነርሱ ምርጫ እልነበረም። እናም እናቲቱ በዚያ መመካቷ ትልቅ ስሕተት ነው። እንደ እኛ ያልሆኑትን ሁሉ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ወይም እንደተረገሙ ማሰብ



እጓጉል ነው። ዛሬ ያልዳኑትን ስናይ ራሳችንን ፀጋ እንደበዛለት ዕድለኛ ሳይሆ ን እንደተለየ ፍጡር ማየት እንዳይጠናወተን ይህ ታሪክ ያስተምረናል። ደግሞም የምናያቸው ነገሮች በእኛ ቁጥጥር ሥር ስላልሆኑ በድንገት ፈጥነው ሊሰዋወጡ ይችላሉ። እዎን ነገሮች ሊገለባበጡ ይችላሉ።

እንዲያውም ይህ ታሪክ ስለ ሐናና ፍናና ከተጻፈው ጋር የሚያመሳስለው ነገር አያጣም። ታዲያ ታሪክ ቀያሪው እግዚአብሔር ነገሮችን ሲገለብጣቸው ሐና እንዲህ ብላ ነበር። "እትታበዩ፥ በኩራትም አትናገሩ፤ እግዚአብሔር እዋቂ ነውና፥ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚመዝን ነውና፥ ከአፋችሁ የኩራት ነገር አይውጣ። የኃያላንን ቀስት ሰብሮአል፥ ደካሞችም በኃይል ታጥቀዋል። ጠግበው የነበሩ እንጀራ እጡ፤ ተርበው የነበሩ ከራብ ዐርፈዋል፤ መካኒቱ ሰባት ወልዳለችና፥ ብዙም የወሰደችው ደከማለች" 1ሳሙ.2፡ 3-5።

## ይድረስ ለእግዚአብሔር

ይህ የሆነው ሜክሲኮአዊው ገበሬ በኃይለኛ የዝናብ እጥረት በተቸገረበት ወቅት ነው። ሰነገሩ ዝናቡ መጣ። ግን በረዶ ቀላቅሎ ወረደና በቆሎውን አውድሞ ሄደ። የመጨረሻ ዘሩን ዘርቷልና እራሱ ምንም አማራጭ አልነበረውም። እዝኖ

በተከራመተበት አንዲት ምሽት ግን ያልጠበቀው አሳብ መጣለት። ስእግዚአብሔር ደብዳቤ ስመጻፍ አሰበ። እናም እንዲህ ሲል በወረቀት ላይ አሰፈረው።

"እግዚአብሔር ሆይ፦ አንተ ካልረዳኸኝ በስተቀር እኔና ቤተሰቤ በዚህ ዓመት መራባችን አይቀሬ ነው። ማሳውን መልሼ ስመዝራትና እስከሚቀጥለው ዓመት ቤተሰቤን ስመመገብ አንድ መቶ ፔሶ ያስፈልገኛል። ይህም ከበረዶው የተነሣ ነው። "

ይህንን ጽፎ በአንቦልክ ካሸገ በኋላ ወደ ከተማይቱ ፖስታ ቤት ገሥገሠ። እዚያም ቴምብር ገዝቶ ስጠፈበትና ከመልእክት ሣጥን ውስጥ ከተተው። መልእክቶችን በማሠባጠር የብዙ ዓመታት ልምድ ያለው አንድ ፖስተኛ ደብዳቤውን ሲያይ በጣም ተገረመ። ይህንን ያህል ዓመት ቢሠራም ስእግዚአብሔር ተብሎ የተላከ ደብዳቤ አጋጥሞት አያውቅምና። ስለዚህ ወስዶ ለፖስታ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አሳየው። ሥራ አስኪያጁ ልቡ እስኪፈርስ ከሳቀ በኋላ ተመልሶ ኮስተር አለ። "እንዴት ያለ ጠንካራ እምነት ነው? ይህንን የጻፈው ሰው እምነት ቢኖረኝ ተስፋዬም እንደ እርሱ ባለ እምነት ቢጸናና ከእግዚአብሔር ጋር እስከ መጻጻፍ ብዘልቅ ምንኛ ደስ ባለኝ!" ሲልም ተናገረ።

በመጨረሻም ደብዳቤውን አንብቦ ከራሱ ምላሽ ሊሰጥ ወሰነ። ፖስታውን ከፍቶ ሲያነበው ግን ከጽሑፍም ያለፈ ተግባር የሚሻ ጥያቄ እንዳዘለ ተረዳ። ስለዚህ ከደሞዙ



የተወሰነውን ከፍል ሰጠና ሌሎች ባልደረቦቹም የሚችሉትን ያህል እንዲያዋጡ አደፋፈረ። በዚያም መሠረት ስባ አምስት ፔሶ አሰባሰበ። እናም በአንቦልክ ከትቶ ከእግዚአብሔር እንደተላከ አድርጎ ፈረመና አሽጎ አስቀመጠው።

በሚቀጥለው ቀን ገበሬው ማልዶ ወደ ፖስታ ቤቱ ደረሰና የ መጣለት ደብዳቤ እንዳለ ጠየቀ። ፖስተኛውም አንቦልኩን አቀበለው። ገበሬው ም ንም የመደነቅ ምልክት አላሳየም። በብዙ መተማመን ገንዘቡን ከቆጠረ በኋላ ግን በጣም ተናደደ። ወዲያውኑም ወረቀትና መጻፊያ ስምኖ ምላሹን ጻፈ። ከዚያም እንደተለመደው ቴምብር ለጠፈና ሣጥኑ ውስጥ ከትቶት ወደ ቤቱ ሄደ። ሥራ አስኪያጁም ፖስታው እንደደረሰው በችኮላ ከፈተው። እንዲህ ይል ነበር። "ከጠየቅሁህ ገንዘብ ውስጥ ስባ አምስት ፔሶ ደርሶኛል፤ የቀረውንም ስደድልኝ። ግን በፖስታ ቤት በኩል አትላከው፤ ም ከንያቱም ሌባ ብቻ ነው እዚያ የተሰበሰበው!"።

## ምን ያስተምረናል?

የገበሬው እምነት አስደናቂ ቢሆንም እመስጋኝነት ግን አልታየበትም። ስባ አምስቱ ፔሶም ቢሆን የደረሰው በፖስተኞቹ እጅ እልፎ መሆኑን ዘንግቷል። ጭራሹኑ ገንዘቡን ያዋጡለት እነርሱ መሆናቸውን ቢሰማማ እንዴት በደነገጠ!

ብዙ ጊዜ የጸሎቶቻችን መልሶች የሚመጡት በሰዎች በኩል ነው። አስቀድመን ያን ላደረገ ለእግዚአብሔር ቀጥሎም ስለታዘዙ ለሰዎች ምስጋና ማቅረብ ይገባናል። እለበለዚያ የአስጨናቂው ዘመን ሰዎች ባሕርይ አንጸባራቂ ልንሆን ነው።

ጳውሎስ ለመንፈሳዊ ልጁ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት ሁለተኛ መልእክት እንዲህ ይላልና። " ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የእምልኮት መልክ ኣላቸው ኃይሉን ግን ከደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ" 3:1-5።

## ትዕቢተኛው ዝኆን

ድርጭቷ እንቁላል ጥላ ዘወር ከማለቷ ዝኆን በዚያ ሲያልፍ ረጋግጦ ይሰብርባታል። እርሰዋም በዚህ ድርጊት ከፉኛ ታዝናለች። እናም አንድ ቀን ሲመለስ ጠብቃ ለምን



እንቁላሎቿን እንደሰበረ ትጠይቀዋለች። እሱም እንደተጀነነ "የአንቺ እንቁላሎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም፤ ደግሞስ ተሰበሩ አልተሰበሩ ምን ለውጥ ያመጣሉ? ስለ አንቺስ እንቁላል ማን ይጨነቃል? " በማለት ይመልስላታል። ድርጭት ከደረሰባትም ሐዘን በበለጠ በዝኆኑ ትዕቢት ተበሳጭታ "ግድየለም አሁን እንዲህ የሆንከው ማንም አይነካኝም ብለህ ነው፤ ግን ለጉልበተኛም ጉልበተኛ እለውና ጥቂት ቀን ጠብቅ" አለችው። ዝኆኑ ግን በድርጭት ድፍረት እጅግ ተገርሞና ስቀባት አልፎ ሄደ።

ድርጭት ነገሩን በጥሞና ካሰበችበት በኋላ በአካባቢዋ ከ ሚኖሩና ረጃጅም መንቆር ካላቸው ወፎች ዘንድ ሄዳ የደረሰባትን መከራ አጫወተቻቸው። ወፎቹም በዝምታ ትረካዋን አዳምጠው ሲያበቁ እጅግ አዝነው እንዲህ አሏት። "እዚህ ሠፈር የሚኖረው ዝኆን የታበየ መሆኑን ሁላችን እናውቃለን፤ ከፍ አድ ርገን በዛፍ ላይ መሰቀላችን በጀን እንጂ የእኛንም እንቁላሎች ከመስበር አይመለስም። በደረሰብሽ ነገር ልባችን ተነክቷል፤ ግን እንዴት እንደምንረዳሽ እናውቅም"። ድርጭትም መልሳ "ከእናንተ የምፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ይኸውም በረጅም መንቆራችሁ ጠቅጥቃችሁ ዐይኑን አጥፉልኝ! ከዚያ በኋላ ያለውን ለእኔ ተውልኝ" አለቻቸው። ወፎቹም ወዲያውኑ በዚህ ተስማምተውና በሚቀጥለው ጧት በአንድነት ከብበው የዝሆንን ዐይን እንደ ተዋጊ አውሮፕላኖች በመመላለስ

ጠቀጠቁ። እርሱም ጨለማ ወደቀበት። ድርጭት ከአካባቢው ሳትርቅ ስትቃኘው ዋለችና እኩለ ቀን ሲሆንና ዝኖኑ ውኃ ሲጠማው ወደ እንቁራሪቶች መንደር አቀናች። ለእነርሱም ዝሆን ያደረሰባትን መከራ ደግሞም እንዴት እንዳሸፈባት አጫወተቻቸው። እንቁራሪቶቹም በዝምታ ትረካዋን አዳምጠው ሲያበቁ ልክ እንደ ወፎቹ ሃዘንዋን ተካፍለው እንዲህ አሏት። "በዚህ ሠፈር የሚኖረው ያ ግዙፍ ዝኖን ከልክ በላይ የታበየ መሆኑን እኛ ሁላችን እናውቃለን። ውኃ ለመጠጣት ሲመጣ የእኛንም እንቁላሎች ከመስበር አይቦዝንም። የደረሰብሽ ነገር ሁላችንን አሳዝኖናል፤ ግን እንዴት እንደምንረዳሽ አናውቅም"። ድርጭትም መልሳ "ከእናንተ የምፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ይኸውም ከዚህ ውኃ ወጥታችሁ ማዶ ካለው ረባዳና ድንጋያማ ገደል ውስጥ እንድትገቡና ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንድትጮኹ ነው " አለቻቸው። እንቁራሪቶቹም የተጠየቁት ውለታ እጅግ ቀላል መሆኑን ለድርጭት ነገሯትና ጊዜ ሳያጠፉ ቦታ ቀይረው መጮህ ጀመሩ። ይህን ጊዜ ዝኖኑ ወንዝ አካባቢ ያለ መሰሎት ውኃ ሊጠጣ እግሮቹን እየጎተተ ወደዚያው ተራመደ። ከዚያም ኸው ካለው ድንጋያማ ገደል ውስጥ ገብቶ ተሰባበረ።

## ምን ያስተምረናል?

የዝኖኑ ጥፋት ሁለት ነው። በመጀመሪያ የድርጭትን እንቁላል ሰብሯል። በሌላ አነጋገር የዘር ማጥፋት



ወንጀል ፈጽሞአል። ያም ሳይበቃ ለምን ብላ ላቀረበ ችው ጥያቄ በማናለብኝነት በመመለስ የባስ አሳዝኗታል። ለዚህም በመጨረሻ የእጁን ያገኘ ይመስላል።

ምንም አያመጡም በሚል ትዕቢት ታናናሾችን መናቅ ብሎም መጉዳት እንደማይገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። "ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእከቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና" ማቴ.18:10። ባለማወቅ ከተፈጸመም ጥፋትን መናዘዝ የግድ ይሆናል። ምን ትፈጥራለህ ማለት በጉዳት ላይ ጉዳት መጨመር ይሆናል። በዚያም ላይ ልክ እንደ ዝኖኑ ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ መዋረድ አይቀርም። "ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች፤ በትሑታን ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች" ምሳ.11:2።

## ዝናብና ጽጌረዳ

ይህ ደግሞ ከተረትና ምሳሌ መጽሐፍ የተገኘ ነው። ግን ታሪኩ በግጥ ም የተከሸነ እንደነበር ማስታወሱ ተገቢ ሲሆን ጸሐፊውም ከበደ ሚካኤል ሳይሆኑ አይቀሩም።

ጽጌረዳዋ አበባ ዝናብ ባለመውረዱ እጅግ ጠውልጋና ከስታ ነበር። ስለዚህም እንገቷን አዘንብላ ለመሞት ስታጣጥር ሳለ ዝናብን ደመና ጭኖ ባለችበት ስፍራ ባለው የሰማይ ትይዩ ሲያልፍ ተመለከተችው። እናም

በደከመ ድምፅ "አባክህ በፀሐይ ሐሩር ደከሜ መሞቴ ነውና ጥቂት አንኳን ውኃ አንጠባጥብልኝ" በማለት ለመነችው። እርሱም "አሁን አልችልም፤ የድንገተኛ እርዳታ ጥሪ ደርሶኝ ወደ ሩቅ አገር እየሄድኩ ነው፤ እንደ ምንም ታግሠሽ ከጠበቅሽኝ ግን የሚበቃሽን ያህል አዘንብልሻለሁ" ብሏት ጉዞውን ቀጠለ። በርግጥም ዝናብ ቃሉን ጠብቆ ከሄደበት ሲመለስ ዶፉን አወረደላት። ግን ያ ውኃ ለምድሪቱና ለሌሎች ዕፅዋት እንጂ ለጽጌረዳ ጥቅም አልነበረውም። ከመጠውለግም አልፋ ደርቃ ነበርና። ዝናብም ሊደርስላት እንዳልቻለ ዐውቆ እያዘነ ጉዞውን ቀጠለ።

## ምን ያስተምረናል?

ጽጌረዳዋ ርዳታውን የምትፈልገው ወዲያውኑ ነበር። ኋላ የመጣው ዶፍ ሊያጠጣት ሳይሆን ሊጠርጋት ነው። ይህንን በእግዚአብሔር ቃል መነፅር ስናየው የመዳን ቀን አሁን ነው የሚለውን ያስታውሰናል (2ቆሮ. 6:2)። አንድ ቀን እነግረዋለሁ የምንለው ወዳጅ ካለን ወንጌሉን ለመስበክ ጊዜው አ ሁን ነው። ሌላ ቀን ላይኖር ይችላል። የሞተም ንስሐ የለውም።

ሌላው ደግሞ ከወዳጆቻችን ጋር ስላለን ሕብረት ነው። "ለተቸገረው ለው በጎ ነገርን ማድረግ አትከልክል፥ ልታደርግለት የሚቻልህ ሲሆን ወዳጅህን ሂድና ተመለስ፤ ነገ አሰጥሃለሁ አትበለው። በጎ ነገርን ማድረግ ሲቻልህ ይለናል



ቅዱሱ ቃል (ምሳ.3:27-28)። አከሎም በጊዜ አንድንሮጥ እና በመልካም አንደንጨርስ ማንም ሊሠራባት የማይችል ሌሊት ትመጣለች ሲል ያነቃቃናል (ዮሐ.9:4)።

## የሾላውና የዱባ ፍሬ

ይህንንም ታሪክ በልጅነቴ ዘመን በግጥም መልክ ተጽፎ ነው ያነበብኩት። ሰውየው የ መንገዱ ርዝመትና የፀሐዩ ብርታት አድክሞት ከአንዲት የሾላ ዛፍ ሥር ይቀመጣል። ቀጥሎም ጋደም ይላል።

ታዲያ አእምሮው አላረፈም ነበርና አንዱን ሲያነሣ አንዱንም ሲጥል ቆየ። በተለይም ከሾላው አጠገብ የበቀለውን ዱባ አተኩሮ ተመለከተ። ቀጥሎም ቀና ብሎ ትልቁ የሾላ ዛፍ የተሸከማቸውን ብይ የመሳሰሉ ፍሬዎች አስተዋለ። በመጨረሻም እንዲህ ሲል አስተያየቱን ሰጠ ። "የዱባው ዛፍ በመሬት የሚጎተት ሐረግ ነው፤ ግን ይባስ ብሎ እንዳች የሚያካክል ፍሬ ተሸክሟል። የሾላው ዛፍ ደግሞ ግንዱ ቢገፉት አይወድቅም፤ ግን ላዩ ላይ ያሉት ፍሬዎች ጉንዳን ነው የሚያካክሉት። ስለዚህ የፍጥረት ስሕተት ተደርጓል። ዱባውን አውጥቶ ከሾላው ዛፍ ላይ መስቀልና እንደገናም እ ነዚያን ደቃቅ ፍሬዎች አውርዶ

መሬት የተኛው ሐረግ ላይ ማስደገፍ ቢቻል ይስተካከል ነበር። "

ይህንና ያንን ሲል ደከሞት የነበረው ተፈላሳፊ መንገደኛ እንቅልፍ ሸለብ አደረገው። ግን ብዙም ሳይተኛ በድንገት ባንኖ ተነሣ። ምክንያቱም አፍንጫው ላይ ሕመም ተሰምቶት ነው። ሲዳብሰውም አፍንጫው መድማት ጀምሮ ነበር። ምን እንደመታው ለማወቅ ዘወር ዘወር ሲል ንፋስ የጣላት የሾላ ፍሬ ያልታሰበ አደጋ እንዳደረሰችበት ተገነዘበ። እናም ያችን ትንሽ ፍሬ ይዞ በመደነቅ እገላብጦ ከተመለከታት በኋላ እንዲህ አለ። "የፈጣሪ ሥራ ምንም ስሕተት የለበትም። እንደ እኔማ ፍልስፍና ቢሆን ኖሮ ይህቺ ያ ግዙፍ ዱባ እናቴን ፈጥፍጦ በገደለኝ ነበር!"

## ምን ያስተምረናል?

መንገደኛው ፈጥኖ የተረዳው ነገር ድንቅ ነው። ልክ እርሱ እንዳሰበው የተክሎቹ ፍጥረት ቢስተካከል ኖሮ ከእንቅልፉ ባልነቃም ነበር። እግዚአብሔር በጥልቅ ጥበቡ ሁሉን ድንቅ አድርጎ ሠርቷል። እኛ የእጆቹ ሥራዎች ነንና መልካሙን ልናደርግ እንጂ የእርሱን ፍጥረት ልንገመግም አልተጠራንም። መብቱም የለንም። መጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት በማይባሉ ሥፍራዎች ይህንኑ ያብራራል።

" አቤቱ፥ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው፤ ሁሉን በጥበብ አደረግህ፥ ምድርም ከፍጥረትህ ተሞላች" መዝ.104:24።



"እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ፥ በማስተዋል ሰማያትን በየስፍራቸው አጸና። በእውቀቱ ቀላያት ተከፈሉ፥ ደመናትም ጠልን እንጠባጠቡ" (ምሳ. 3፡ 19-26)። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣም "ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን" ይላል (ሮሜ 16:27)። አሜን!

## የሚሊዮን ዶላር መድኅን

ባለጠጋው በሰገነቱ ላይ ቆሞ ው ድ ሽቀጥ የጫኑት ስድስት መርከቦቹ በሰላም የመመለሳቸውን ወሬ ይጠባበቃል። ግን የደረሰው ቴሌግራም ያንን የሚያጠናክር አልነበረም። ይልቁንም ኃይለኛ የውቅያኖስ ማዕበል በመነሣቱ የመርከቦቹ ደኅንነት አደጋ ላይ መውደቁ ተሰማ። ይህን ጊዜ ባለ ሀብቱ ወደሚመለከታቸው ስልክ ደወለ። ሁኔታው እየተሻሻለ ከመሄድ ይልቅ እየባሰበት መምጣቱን መርከቦቹም በሰላም መድረሳቸው አጠራጣሪ መሆኑንና ቢደርሱም እንኳ ከታሰበው ጊዜ በጣም ሊዘገዩ እንደሚችሉ ከዋናው የወደብ አስተዳዳሪ ተረዳ።

ይህን ጊዜ ቶሎ ብሎ አማካሪውን አስጠራ። ሁኔታውንም አዋየው። በዚህ የተካነው ባለሙያም በነገሩ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ካሰበ በኋላ እንዲህ አለ። "ስለ

ማዕበሉ ልናደርግ የምንችለው እንዳች ነገር የለም፤ የውቃውን ነውጥ ልንቀለቅሰውም ይሁን ልናቆመው ሥልጣን የለንም። ስለዚህ ማሰብ ያለብን ስለ መርከቦቼ ብቻ ነው። እናም ብቸኛው አማራጭ ለመርከቦቼ የመድኀን ዋስትና መግዛት ይሆናል። በአንድ ሚሊዮን ዶላር ለስድስቱም መርከቦች ሙሉ ዋስትና መግዛት እንችላለን። አይበለውና ሁሉም ቢሰጥሙ እንኳ ሙሉ ዋጋቸውን መልሰን እጃችን እና ገባለን፤ እዎን ብቸኛና የሚያዋጣ ምርጫችን እርሱው ነው። የአንድ ሚሊዮን ዶላር ዋስትና! ”

ባለሀብቱም አማራጭ በማጣቱ በዚሁ አሳብ ተስማማና አንድ ሚሊዮን ዶላር ፈቀደ። ዋስትናውም ተገዛ። ግን ብዙም ሳይቆይ ነገሮች መሻሻል ጀመሩ። ማዕበሉም ቀስ በቀስ ጉልበቱ እየላላ ሄደ። ይህ ፋታ የለጣቸው ባሕረኞች ደግሞ የመርከቦቹን ጉዞ አቃንተው በሰላም ወደ ወደቡ ደረሱ።

ይህንን ዜና በጉጉት የተከታተለው አማካሪ ወዲያውኑ መልካሙን ዜና ለባለሃብቱ አበሰረው። ባለ መርከቡ ግን ምንም የመደሰት ወይም የመገረም ምልክት አላሳየም። እንዲያውም ጠረጴዛውን በቡጢ ደልቆ ሲያበቃ “ቸኩለን የመድኀን ዋስትና ባንገዛ ይሻል ኖሯል ለካ? አሁን ምንም ጠቀመን ከተባለ መልሱ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ኪሣራ ነው” አለና ለራሰ ምታቱ ኪኒን ፍለጋ ሄደ።



## ምን ያስተምረናል?

የዓለማችንን ቁጥር አንድ ባለጠጋ ቤተሰብ የማግኘት ዕድል ገጥሞኛል። ሰዎች ሃብትን ባከማቹ ቁጥር የበለጠ የሚለሰቱበት ምክንያት ግን እስካሁንም አልገባኝም። ይህ ሰው የመርከበኞቹ ሕይወት መትረፍ የቤተሰባቸው ደስታ አልታየውም። ማዕበሉ ጋብ በማለቱ በሰላም የደረሱት ሌሎች መርከቦችና ተጓገሮች ደኅንነት ምንም አልመሰለውም። የእርሱ ልብ ያለው አንድ ሚሊዮን ዶላር ላይ ነውና።

ልክ እንደዚሁ ሰው በ ሕይወት ለለመኖራቸው ከማመስገን ይልቅ ካልሲ ለለጠፉባቸው የሚያማርሩ ጥቂት አይደሉም። በሽታቸውም ፍቅረ ንዋይ ይባላል፡ ገንዘብን ከልክ በላይ መውደድ እንደማለት ነው። ገንዘብ ከተቆጣጠሩት ጥሩ አገልጋይ ጌታዬ ካሉት ግን ጨካኝ አለቃ እንደሆነ ዐዋቂዎች ይናገራሉ። ቅዱስ ቃሉ እንደሚል የከፉ ከንውኖች ሁሉ ምንጭም ነው። “ገንዘብን መውደድ የከፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ እንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ” 1ጢሞ.6:10።

## አቧራን ማራገፍ

ግለሰቡ አህያውን ለዘመናት ተገልግሎበታል። አሁን ግን አህያው በዕድሜ በመግፋቱ ሁለት ችግሮች ተፈጠሩ።

በመጀመሪያ አቅሙ ስለደከመ ዱሮ የሚሸከመውን ያህል መጫን እልተቻለም። በዚያ ላይ ፍጥነቱ እጅግ ቀስስተኛ በመሆኑ ብዙ ሰዓት እየፈጀ ነው። ስለዚህ ግለሰቡ ሌላ አህያ ለመግዛት ማሰቡ ግድ ነበር። ያዘገየው በቂ ገንዘብ እጁ ላይ አለመኖሩ ብቻ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ አንድ ቀን አህያው ከነሸክሙ ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ። ባለቤቱም ያሸከመውን ዕቃ ለይቶ ከጉድጓዱ ካወጣ በኋላ አህያውን ለመንተት ሞከረ። ግን ጥቂት እንደጣረ አንድ አሳብ መጣለት። አህያው ያረጀ እንደመሆኑና ሌላ ሊገዛ እንደማሰቡ መጠን አሁን እሱን ለመንተት በ መሞከር አቅሙን መጨረሱ አስፈላጊ አይደለም። ስለዚህ አዚያው ትቶት ሊሄድ ወሰነ። ግን ደግሞ ብዙ ዓመት አገልግሎታልና የእውሬ እራት ከሚሆን ይልቅ ጉድጓዱን በአፈር ሞልቶ በቁሙ ሊቀብረው ፈለገ። ስለዚህ ጥቂት ግለሰቦችን ለምኖ አፈር በአካፋ እየዛቁ ወደ ጉድጓዱ መወርወር ጀመሩ።

አህያው ለዘመናት አገልግሎቱ የተሰጠው ምላሽ ከነሕይወቱ መቀበር መሆኑን ሲያይ በጣም አዘነ። ግን አዝኖ አልቀረም። በበኩሉ አንድ መላ መታ። ይኸውም አቧራውን ማራገፍ የሚል ነበር። እናም አንድ አካፋ በተወረወረበት መጠን እርሱም እላዩ ላይ የሚያርፈውን ማራገፍ ጀመረ። ያ ደግሞ አስደናቂ ውጤት አመጣ። ጉድጓዱ በሞላ መጠን



እህያውም ከፍ ማለት ጀመረ። በመጨረሻም ጉድጓዱ በአፈር ሲሞላ አህያው ተራምዶ መውጣት ቻለ።

## ምን ያስተምረናል?

በርግጥም አህያው በባለ ቤቱ ጭካኔ የተሞላበት ውሳኔ አዝኖ ቢቀር ኖሮ በቁሙ በተቀበረ ነበር። ግን ያንን ትቶ ምን ማድረግ እንዳለበት ማሰቡ ከሞት አተረፈው። በደረሰባቸው መገፋት እየቆዘሙ ዛሬን መኖር ያቆሙ ብዙ ናቸው። ትናንትን እያሰቡ ዛሬን ማበላሸት ሞኝነት ነው። ማርጀትህን የምታውቀው በትዝታ መኖር ስትጀምር ነው የሚል አባባል አለ። በመንፈሳዊ ሩጫም ቢሆን የደረሰብንን ስደትና መከራ ሳይሆን ሊገለጥ ያለውን ክብር እያሰብን ወደፊት መቀጠል አለብን። ጳውሎስ የገባው ከዚህም ያለፈ ነው። መልካሙን ልምምድ እንኳ ስተርከው አልኖርም፤ የበለጠውን እጨብጥ ዘንድ እየረሳሁት እገሠግሣለሁ ይለናል። "እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ። አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤

በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ"
ፊልጵ.3፡ 10-13።

## ወንዙን መለማመጥ

መንገደኛው ከረጅም ጉዞው አጋማሽ ላይ የሚሻገረው ወንዝ ነበረው። ግን እዚያ ሲደርስ ኃይለኛ ዝናብ ወርዶ ወንዙ ጢም ብሎ ሞልቶ ጋላቢ ጎርፍ ሲወርድበት አየ። ድልድይ ወይም ሌላ ማቋረጫ አልነበረምና ያለው ብቸኛ አማራጭ ውኃው እስኪጎድል ቆሞ መጠበቅ ብቻ ነበር። እናም ሌሎች መሙላቱን ያዩ ዞረው ወደመጡበት ሲመለሱ እርሱ ግን መሰንቆውን ይዞ ዜማ መደርደር ጀመረ።

ጥቂት ለማይባል ጊዜ እንዲያ ካደረገ በኋላ ከአንድ ተመልካች እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበለት።

"እዚህ ምን ታደርጋለህ?"

"ምናልባት ወንዙ በዜማዬ ራርቶ ቢያሻግረኝ ብዬ እየደረደርኩ ነው"

"እይ ሞኝነት! ለመሆኑ ወንዝ ከመቼ ወዲህ ነው መስማትና መራራት የጀመረው? ይሰማል እንኳ ብለን ብናስብ የውኃውን አወራረድ መመልከት ያሻናል። ያልሰማው ሲመጣ የሰማው እየሄደ እኮ ነው ያለው " አለ ጠያቂው በመገረም።

### ምን ያስተምረናል?

ጠያቂው እንዳለው ወንዙ ባለመሰንቆውን የመስማት ብቃት አልነበረውም። እና ይህ ታሪክ ለማይሰሙ ነገሮች ችግራችንን በማዋየት ዕድሜያችንን እንጨርስ ነው የሚለን። ሚሊዮኖች ቢትና ማታ አቤቱ የሚሏቸውን ግን እንኳን ሌላውን ራሳቸውን ማዳን የማይችሉትን አማልክት የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ያቀርባቸዋል። " የአሕዛብ ጣዖታት የብርና የወርቅ፥ የሰው እጅ ሥራ ናቸው። አፍ አላቸው፥ አይናገሩምም፤ ዓይን አላቸው፥ አያዩምም፤ ጆሮ አላቸው፥ አይሰሙምም፤ እስትንፋስም በአፋቸው የለም። የሚሠሩአቸው ሁሉ የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁን (መዝ.135፡15-18)።

ጨረቃና ከዋከብት ወንዞችና ዛፎች ግዑዛን ናቸውና እንኳን ሰውን ሊረዱ (ዱ ይጠብቃል) ራሳቸውም ረዳት ይሻሉ። ከ እነርሱ ጆርባ ሰምቶ የሚመልስ የለም። ቢኖርም እንኳ ያ የአጋንንት አሠራር ነው። ብዙዎች ግን ይሰሙናል ብለው ይሰግዱላቸዋል። ለ እነርሱም ያጥናሉ። ይህም ለምን ሆነ ብለን አንገረምም። ምክንያቱም ዘመን የማይሽረው የጌታ ቃል "ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ

ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ ብሎናል" (2 ቆሮ.4:4)።

## ማነው ባለጠጋ?

ንጉሡ የአገሩን ከተሞች እየተዘዋወረ ይጎበኛል። አንዳንድ ዜጎችንም ያነጋግራል። ግን ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን ዕውቀት ሳይጠይቅ አይተዋቸውም። ታዲያ አንዱን ቀን ሃብታሞች በሚበዙበት አካባቢ አለፈ። ምርጥ ፈረስ የሚጋልበውን ሰው አስቀድሞ እንዲህ አለው።

"እግዚአብሔርን ታውቀዋለህ?"

"አላውቀውም!"

"ያሳዝናል፤ ሃብታም ስትመስል ድሃ ነህ!"

ትንሽ ተጉዘም ሌላውን ጥሩ የለበሰ ሰው አግኝቶ እንዲህ አለው።

"እግዚአብሔርን ታውቀዋለህ?"

"አላውቀውም!"

"ያሳዝናል፤ ሃብታም ስትመስል ድሃ ነህ!"

ያናገራቸው ሁሉ የሞላላቸው ሃብታሞች ነበሩ። በስተመጨረሻ ግን አንድ ምስኪን ድሃ አገኘ። እንዲህ ም አለው።

"እግዚአብሔርን ታውቀዋለህ?"



"አዎን አውቀዋለሁ!"

"ይገርማል፤ ድሃ ስትመስል ሃብታም ነህ!"

### ምን ያስተምረናል?

ኢየሱስ በትምህርቶቹ የሰው ማንነቱ ከሃብቱ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ብሏል (ሉቃ.12:15)። ገንዘብ የዘላለምን ሕይወት አይገዛም። አማኞች የሌላቸው ቢሆኑ እንኳ ሌላውን የማበልጠግ ብቃት ተሰጥቶአቸዋል። እግዚአብሔርም የሚያያቸው እንደዚያ ነው። "መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፤ ነህ ግን ባለጠጋ ነህ" (ራዕ.2:9)።

## የረዳት ያለህ!

ሰውየው በተራራ ጫፍ ላይ እየተጓዘ ሳለ ይንሸራተትና ቁልቁል ይወድቃል። ግን ታች ወርዶ ከመፈጥፈጡ በፊት ተራራው ወገብ ላይ የበቀለች ዛፍ ያገኝና እርሷ ላይ ይንጠለጠላል። ሆኖም ጥቂት እንደቆየ እጁ እየዛለ ሲሄድ አማራጮቹን ማሰላሰል ያዘ። ኸው ብሎ ወደ ታች ከወረደ የመትረፍ ዕድል አይኖረውም። ከርቀቱና ከዳገቱ ቀጥተኛነት የተነሣ ወደ ላይ ለመንጠልጠልም የአንድ ሰው አቅም አይበቃም። እናም የሚያልፍ ሰው እንደሚሰማው

ገመድም እንደሚሰድድሰት ተሰፋ በማድረግ እርዳታ ፍለጋ መጮኹን ቀጠለ። " እዚያ ላይ አባካችሁ እርዱኝ" እያለ ለረጅም ጊዜ ቢጣራም ሰሚ አላገኘም። ተሰፋ ቆርጦና አቅሙም ተሟጦ ዛፉን ሊለቅቀው ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀር ግን ድምፅ ከላይ መጣ።

"ጃክ፤ ትሰማኛለህ?"።

"አዎን ይሰማኛል፤ እዚህ ታች ነው ያለሁት"።

"እይሃለሁ ጃክ፤ ግን ደህና ነህ?"።

"አዎን ደህና ነኝ፤ ግን አንተ ማን ነህ? የትስ ነው ያለኸው?"።

"እኔ አምላክህ ነኝ፤ ሁሉም ቦታ አለሁ"።

"አምላክ? እግዚአብሔር ነህ ማለት ነው?"።

"አዎን!"።

"እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ እርዳኝ። ከዚህ ብታወጣኝ ደግሜ ኃጢአት አልሠራም። ጥሩ ሰው እሆናለሁ። ዕድሜዬን ሁሉ አገለግልሃለሁ!"።

"አሁን ቃል አትግባ ጃክ፤ መጀመሪያ ላውጣህና በኋላ እንነጋገራለን። አሁን እንድታደርግ የ ምፈልገውን ልንገርህ"።

"እዘዘኝ ጌታ ሆይ፤ ያልከኝን ሁሉ አደርጋለሁ"።

"መልካም፤ ዛፉን ልቀቀው!"

"ምን?"



"ዛፉን ልቀቀው ነው ያልኩህ፤ በ እኔ ተማመን፤ ልቀቀው!"

ለጥቂት ጊዜ ፀጥታ ከሆነ በኋላ የጃክ ድምፅ ተሰማ።

"እዚያ ላይ፤ አባካችሁ እርዱኝ!"

## ምን ያስተምረናል?

ሰዎች ያድነናል ብለው የጨበጡትን ነገር መጣል አይሆንላቸውም። ሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ደግሞ በእኔ ብቻ ታመኑ ይላል። እዚያ ላይ ነው መተላለፍ የሚመጣው። የሁሉን ቻዩን አምላክ ረድዔት ለመቀበል ሰንፈልግ ትዕዛዙንም መቀበል የግድ ይሆናል። ረድዔቱ የሚመጣው እርሱ ባሰቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንጂ እኛ ባሰመርነው ላይሆን ይችላልና።

ለዚህም ይመሰላል ቃሉ "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል። በራስህ አሰተያየት ጠቢብ አትሁን፤ እግዚአብሔርን ፍራ፥ ከክፋትም ራቅ" የሚለው (ምሳ.3:5-7)።

# እንሰናበት

አንባቢ ሆይ ጊዜዎትን ሰጥተው የገበታ ወጎቻችንን ስላነበቡ ከፍቅር ካፌ ምስጋናዬ ይድረሰዎ። እርግጠኛ ነኝ

በቆይታዎ ምድራዊውን ታሪክ እየለቀምን እንዴት ወደ ሰማይ መዳረሻ እንዳደረግነው በሚገባ ታዝበዋል። ደግሞም እዚህ ግቡ የማይባሉ የመሬት ወሬዎችን ሰብስበን መንፈሳዊ ማሠሪያ እንዳበጀንላቸው ደጋግመው ቃኝተዋል። ይህ ደግሞ ያለምክንያት አይደለም፤ የስንዝሮን ታሪክ እየለማ አድጎ አለተሳሰቡ እንደ ሰንዝሮ ቁመት ያጠረውን ትውልድ ስሕተት ላለመድገም ነው። የማይሻረው የእግዚአብሔር ቃል የሚታየው ጊዜአዊ የማይታየው ግን ዘላለማዊ እንደሆነ አስረግጦ ነገሮናልና። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ በርካታ ታሪኮችን እንደ ምሳሌ እየተጠቀመ ያስተምር እንደነበር ማጤናችንም ለዚሁ ትልቅ መገለጥ በሩን ወለል አድርጎ ከፍቶልናል።

ጊዜውን ሳይነፍግ ለሰጠዎ የዘመናት ጌ ታ ታላቅ ሞገስ ይሁንና እነዚህን ትንንሽ ታሪኮች ሲያነቡ ይልቁንም በአተረጓጎማቸው ከፍ ሲሉ ቆይተው እነሆ ጨረሱ። መልካም አድርገዋል። ግን ከመሄድዎ በፊት እኔ እዘጋጁ እንድ አከብሮት ያልተለየው ጥያቄ ባቀርብልዎ ደስ ይለኛል። በተረት ተረት ሳይሆን በመስቀል መሥዋዕትነት ለተበጀችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ራስዎን እዘጋጅተዋል? ከሆነ እሰየው መንገድዎን በጥንቃቄ ይቀጥሉ። ካልሆነ ግን ይህንን ወርቃማ ዕድል ይጠቀሙበት። በመጨረሻ እንዳነበቡት የጃከ ታሪክ ያድነኛል ብለው የተጠመጠሙበትን ተሰባሪ ነገር ይልቀቁና የሕይወት ዛፍ በሆነው በኢየሱስ ላይ ይጣበቁ። እነሆ



ከዚህች በታች የሠፈረችውን አጭር ጸሎት በመድገም ጉዞዎን በልበ ሙሉነት ይጀምሩ።

"እግዚአብሔር ሆይ ስለ እኔ ኃጢአት ልጅህ በመስቀል እንዲሞት ስለፈቀድክ ተመስገን። በደሌን ይቅር በለኝ። በክርስቶስ አዳኝነትና ጌትነት አምኛለሁ። እስከ ዛሬ የኖርኩትን ያለማወቅ ሕይወት ግን ከጄአለሁ። እንደ ተስፋህ ስሜን በሕይወት መዝገብ ጻፈው። ከዛሬ በኋላ እንደ ቃልህ እንድኖር እርዳኝ። በኢየሱስ ስም አሜን!"

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንኳን ደህና መጡ። እንደ ፍቅር ካፌ ምግብ ቆይቶ ከሆድ በማይጠፋው የአምላካችን ቃል ራስዎን ይመግቡ። እንደ እርስዎ ከሚያምኑ ጋርም ሕብረትን ያድርጉ። እገር ምድሩን እየዞርኩ ያልተሸቀጠ ወንጌል መስበክና ማስተማር ጀምሬአለሁና ንጉሡ ከፈቀደ በምድር አንድ ቀን እንተያይ ይሆናል። እልያም በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም በሚደረገው የበጉ ሠርግ እራት ላይ እስክንገናኝ ሰላም ይሁኑልኝ።

በእግዚአብሔር እምሳል የተፈጠሩ ሰዎች እንብበው ሲድኑ፣ እንብበው ሲጸኑ ብሎም ሲጽናኑ ማየት ደስ የሚያሰኘው እልፎም የሚያስፈነድቀው ወንድምዎ ዓለማየሁ ማሞ ነው።

## አስተያየት

በቤት ውስጥ ባለን የእብሮነትና የእራት ጊዜ ላይ ዓሌክስ የሚተርክልን ተረቶች በርካታ ና ቸው። ብዙዎቹ

እዝናኞች ብቻ ሳይሆኑ ትምህርት ሰ ጪዎችም ስለሆኑ ባለቤቴን እንድ ላይ አጠራቅሞ እንዲያሳትማቸውና ለተተኪው ትውልድ ተጽፎ እንዲቀመጥ ሰላበረታታሁት በዚሁ መሠረት መጽሐፉን ለማዘጋጀት በቅቷል።

ፍቅር(ተ) ታደሠ

# አ በ ር ከ ቶ ት

የመጽሐፉ እበርከቶት ለኤፍሬም ዓለማየሁ እንዲሆን ወሰኛለሁ።

የዘጠኝ ዓመቱ ልጄ የተዋጣለት ተራኪ ነው። “ዶሮዋ በከተማ” የሚለውና በዚህች ጥራዝ ውስጥ ለናሙናነት የተጨመረው የእርሱ ትረካ በምድር እስካለሁ ፈጽሞ የምዘነጋው አይደለም። በሚጣፍጠው እንደበቱ እጆቹን እያወናጨፈና ዐይኑን እያሰለመለመ ሲነግረን በጣም እመሰጥ ነበርና ደጋግሜ እንዲነግረን ጠይቄዋለሁ። እርሱም በብዙ ደስታ ታዝዞ ያንኑ አድርጓል።

እናም የዚህች ለየት ያለች መጽሐፍ መታወሻነት ለእርሱ መሆኑ ተገቢ ነው። ለ ኤ ፍ ሬ ም ዓለማየሁ!



## ሁለቱ ከዋክብት

በፍቅር ካፌ የዘወትር ታዳሚዎችና የታሪኮቹም ቀዳሚ አድማጮች የሆኑት የዓለማየሁ ልጆች ርብቃና ኤፍሬም እነዚህ ናቸው። በዚህ አጋጣሚም ርብቃና ኤፍሬም ጊዜ ወስደው በመጽሐፉ ጀርባ ላይ የሰፈረውን እለተያየት ለለጻፉ ደራሲው (ምድራዊ እባታቸው) ሊያመሰግናቸው ይወዳል።



## ለማሳወቅ ያህል

በበርካታ መጻሕፍት ዝግጅት ሥራ ላይ የመሳተፍ ዕድል ስለተሰጠኝ ደስተኛ ነኝ። ጽፌአለሁ፡ ገጥሜአለሁ፤ ተርጉሜአለሁ፡ እንዲሁም አርሜአለሁ። አሁን ደግሞ ይኸው የጓዳችንን ወጎች አካፈልኩ። ከነዚያ መሃል የሕትመት ብርሃን ያዩና እንባቢያን እጅ የገቡ ከሠላሳ በልጠዋል። በዚህች በመጨረሻዋ ገጽ ሲሦዎቹን ልዘርዝር...

ድርሰትና ዝግጅት

1) ኑሮ በአሜሪካ
2) ልጆችን ወደ እውነት መምራት
3) እነማን ነበሩ?
4) የማዕበል መንገደኞች

ትርጉም

5) የወጣትነት ጥያቄዎች
6) የብርታቱ ምሥጢር

እርትዖትና እርማት

7) ሾተልና መስቀል
8) የጋብቻ እንቆቅልሽ

ግጥም

9) የዘመኑ ሰው
10) ለተሰጠኝ ዕድሜ

የኣኔ፡ኣማርኛ፡ችሎታ፡በኣገሬ፡ታሪካች፡
ተሻሽሏል። እናንተ፡ሰዎች፡ ለልጆቻ
ችሁ፡የኣለማየሁ፡ማሞን፡መፃህፍት፡
ኣንብቡላቸው። -ኤፍሬም፡ኣለማየሁ።

ከገቴ፡ደማ፡ካጆርማዋል፡ያሄን፡መዐደሃፍ፡
ስለየሄ። ካሔን፡ዳስ፡ካሰኝቶኛል።
ብዙ፡ትምህርቶች፡በነዚህ፡ታሪኮች፡
ወስጥ፡ካሉ። ካገቴ፡ካሁቱን፡በልቶ፡ሰጪ
ርስ፡ያተርፍልን፡ነበር። ካናንተ፡ካንዶኔ፡
ታሪኮቹን፡ካንዳት ወደ፡ካመኛለሁ።

-ርብቃ ካለማየሁ



ተራኪው ዓለማየሁ ማሞ የሕትመት መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኛ፤ ደራሲና ተርጓሚ ነው።
ከባለቤቱ ፍቅር(ተ) ከልጆቹም ርብቃና ኤፍሬም ጋር በአሜሪካ የሜሪላንድ ክፍለ ግዛት ይኖራል። ባለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ለጠቅላላ ዕውቀት የሚጠቅሙና ይልቁንም ለነፍስ ዕውቀት የሚበጁ በርካታ መጻሕፍትን አዘጋጅቷል።

ዋጋው 10 ዶላር

$10.00
ISBN 978-1-61119-130-1
51000>
9 781611 191301